# የገጠር መሬት አለመግባባት የሚፈታባቸው መንገዶችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በአማራ ክልል

በሪሁን አዱኛ ምህረቱ*

**መግቢያ**

መሬት በተፈጥሮ የተገኘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሆኑም በላይ ሌሎች የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንበረቶችን ለማፍራት አስፈላጊ የሆነ መተኪያ የሌለዉ ሀብት ነው፡፡ ይህን ሀብት ለማስተዳደርና አጠቃቀሙን ለማሳለጥ የሚያገለግሉ በክልላችን የህግ መዕቀፎች ወጥተው እየተሰራባቸው ይገኛል። የሕግ መዕቀፎቹ መሬት የሚገኝባቸውን፣ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍባቸውን እና የመሬት ባለይዞታነት ቀሪ የሚደረግባቸውን እንዲሁም የአስተዳደር አካላትንና የባለይዞታዎችን መብትና ግዴታዎች ያካትታሉ። የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መብት ጥበቃ በሕግ በበቂ ሁኔታ መደንገጉ ብቻ በቂ አይደለም። ይልቁንስ መብቶቹ በሚጣሱበት ጊዜ አጥፊዎችን ለማረምና መብቱን መልሶ ለማስከበር እንዲቻል ለማድረግ ፍትህ የማግኘት መብት መደንገጉ መብቱን አስተማማኝ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

አለመግባባት ሁልጊዜም በሰዎች መካከል የሚኖር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተት ነው። ሰዎች አለመግባባታቸውን በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ሊፈቱ ይችላሉ። በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሌላ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት አቅርበውም ሊያስወስኑ ይችላሉ። የክልላችን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎች በቅድሚያ ለአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች እውቅና ይሰጣሉ። ከዚህም አልፎ አለመግባባቶች በተቻለ መጠን በዚህ መንገድ ቢያልቁ የሕጎቹ ጽኑ ፍላጎት ነው። ይህ ካልተሳካ ወይም ባለጉዳዮች ይህን ዘዴ ካልፈለጉ አለመግባባቶች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እልባት ያገኛሉ። ሆኖም በተግባር በፍርድ ቤቶች ዘንድ የገጠር መሬት አለመግባበትን በተመለከተ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ድንጋጌዎችን በአግባቡ ያለመረዳት፣ ከዚህ የተነሳ የአማራጭ የሙግት መፈቻ ዘዴዎችን ሚና ለይቶ ያለማወቅ፣ ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ በአግባቡ ጭብጥ ይዞና በተገቢው ማስረጃ አጣርቶ ያለመወሰን እና ተያያዥነት ያላቸው ችግሮች ይስተዋላሉ።

ስለሆነም በዚህ አጭር ጽሑፍ በዋናነት ከገጠር መሬት ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ እንመለከታለን። በተጨማሪም ተደጋግመው ከሚከሰቱ ችግሮች በመነሳት የገጠር መሬት ክርክርን በተመለከተ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለመዳሰስ ይሞክራል፡፡

---

*(LLB ፣ LLM) ቀደም ሲል በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትሕ አካላት ባለሙዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት አሰልጣኝ ሆኖ ሠርቷል። በአሁኑ ጊዜ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። (ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ/ም)

# ፩. የገጠር መሬት አለመግባባት የሚፈታባቸው መንገዶች

## ፩.፩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች

አማራጭ የሙግት መፍቻ ሰዎች በንግድ ግንኙነት፣ በቤተሰብና በሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነታቸው ውስጥ የሚከሰቱትን አለመግባባቶች ለመፍታት በራሳቸው ፈቃድ ወይም በፍርድ ቤት ድጋፍ የሚጠቀሙበት የልዩነት መፍቻ ዘዴ ነው።[1] አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ በፍርድ ቤት ክርክርን ከመፍታት ጋር ሲነጻጸር በርካታ ጥቅሞች አሉት።[2] ፈጣን በመሆኑ ጊዜ እና ወጭ ቆጣቢ ነው። የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን መጨናነቅም ይቀንሳል። በባለጉዳዮች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የሰጥቶ መቀበል መርህን የያዘና የመጨረሻው ስምምነት ላይ እስከሚደርስ ድረስ አስገዳጅነት የሌለው ነው። ግንኙነትን ወደፊት እንዲዘልቅ ያደርጋል። ባለጉዳዮችን አሳታፊና ሚስጥራዊነትን የጠበቀ ነው። በአብዛኛው በባለጉዳዮች የሚመረጥ ሶስተኛ ወገን ሀሳብ የሚያቀርብበት ወይም በፈለጉት መንገድ የሚወሰንበት ሁኔታ በመኖሩ ሁለቱም ወገኖች አሸናፊ የሚሆኑበትን (win win) ውጤት ያመጣል።

በአለም ላይ የተለመዱ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት አይነቶች የሚባሉት ድርድር (negotiation)፣ ዕርቅ (conciliation)፣ ሽምግልና (mediation) እና የግልግል ዳኝነት (arbitration) ናቸው። በእኛ ሀገር የሕግ ማዕቀፍ ግን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3307 - 3347 ያሉት ድንጋጌዎች እውቅና የሚሰጡት ለድርድር፣ እርቅና የግልግል ዳኝነት ነው። ይኸውም ዕርቅና ሽምግልናን ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው አድርጎ መውሰዱን እንገነዘባለን።[3] በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የተመለከቱት አገላለጾች በመጠኑ ግራ የሚያጋቡ ቢሆንም የእንግሊዝኛውን ቅጅ እና የእያንዳንዱን ድንጋጌ ይዘት እንዲሁም የአለምአቀፉን የሕግ ፍልስፍና በመዳሰስ አገላለጾቹን በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 3307 - 3317 ያሉት ድንጋጌዎች ድርድርን (negotiation or compromise)፣ ከቁጥር 33018 - 3324 ያሉት ድንጋጌዎች እርቅ ወይም ሽምግልና (conciliation or mediation) እና ከቁጥር 3325 - 3347 ያሉት ድንጋጌዎች የዘመድ ወይም የግልግል ዳኝነት (arbitration) የሚመለከቱ ናቸው።

ድርድር ማለት ጥቅም አለን የሚሉ ወገኖች የሶስተኛ ወገን ጣልቃገብነት ሳያስፈልጋቸው ወይም የሶስተኛ ወገን ተሳትፎ በጣም ትንሽ ሆኖ (ለምን አትደራደሩም ብሎ መምከር ብቻ) ራሳቸው ሀሳባቸውን በነጻ ፍላጎት በማንሸራሸር ከአንድ የጋራ ጥቅም ከሚያስጠብቅ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ስርዓት ነው።[4] በፍትሐብሔር ሕጉ ድርድር ማለት ተዋዋይ ወገኖች አንዱ ለአንዱ አንድ ነገር ትቶ ወይም ሰጥቶ የተጀመረውን ክርክር ሚያቆሙበት ወይም የሚፈጥረውን ክርክር አስቀድመው የሚያስቀሩበት አንድ ውል ነው።[5]

---

[1] ብርሀነ አሰፋ፣ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓትና ህገ-መንግስቱ፣ *የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (2000ዓ/ም፣ ያልታተመ)*፣ ገጽ 6

[2] ዝኒከማሁ፣ ገፅ 8 እና 9)፤ See also Shipi M. Gowok, Alternative Dispute Resolution in Ethiopia' a Legal Framework, p. 266 - 268, avialable at *www.afrrevjo,net/journal/multi-dicipline/Vol/2/No/2/Art/17/GOWOK.pdf* (accessed on Junly 24/2014)

[3] ሽምግልና እና ዕርቅ በተለያዩ ጽሁፎች ላይ መጠነኛ ልዩነት እንዳላቸው ከሚገልጽ በስተቀር ተመሳሳይ ናቸው። ሽምግልና ተሸማጋዮችን ውጤት ላይ እንዲደርሱ የሚያግዝ ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ያለበትና የሶስተኛ ወገን አስተዋጽኦም ተሸማጋዮቹን እንዲስማሙ መልካም ውጤት ላይ እንዲደርሱ መገፋፋትና መጎትጎት ነው። See, Adriana Herrera & Maria Guglielma da Passano, Land Tenure Alternative Conflict Management, Food and Agriculture Organization of the United Nations, Rome, (2006, p. 84)፤ በዕርቅ ጊዜ የሶስተኛው ወገን ሰው ሚና አስታራቂ ሀሳብ (proposal) እስከማቅረብ የሚደርስ ሲሆን በሽምግልና ጊዜ አሸማጋዩ እንዲስማሙ መጎትጎት እንጂ ሀሳብ የማቅረብ መብት አይኖረውም። (ብርሀነ አሰፋ፣ ማስታወሻ ቁጥር ፣ ገጽ 31 ይመለከቷል።)

[4] Ibid, p. 81

[5] *የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ፣ ኔጋሪት ጋዜጣ፣ 1952 ዓ/ም* (ከዚህ በኋላ የፍ/ሕ/ቁ እየተባለ የሚጠራ) ቁጥር 3307

ዕርቅ ማለት ደግሞ ተስማሚዎቹ ወገኖች በሶስተኛ ወገን አጋዥነት (አስገዳጅ ያልሆነ አስታራቂ ሀሳብ አቅራቢነት) አለመግባባታቸውን የሚፈቱበት ዘዴ ነው::[6] ይኸውም እርቅ በታራቂ ሰዎች ነጻ ፈቃድ መሰረት አንድ ገለልተኛ የሆነ ሰዉ እንዲያስታርቃቸው ፈቃደኛ ሲሆኑ የሚተገበር የሙግት መፍቻ ስርአት ሲሆን የአስታራቂው ሚናም ታራቂዎቹን ማሳመን ወይም አስተያየቶችን መስጠት ብቻ ነው። በእርግጥ አስታራቂው ታራቂዎቹ ስምምነት ላይ እንዲደርሱለት በግልም ሆነ በጋራ እያነጋገረ የማሳመን ስራ ይሰራል። በፍትሐብሔር ሕጉም ዕርቅ ከድርድር የሚለየው በውይይቱ የሶስኛ ወገን አስማሚ ጣልቃ መግባት ነው::[7] ሶስተኛው ወገን አስማሚ በራሱ ውሳኔ መስጠት አይችልም:: ይልቁንስ ባለጉዳዮችን አግባብቶ ስምምነት እንዲፈርሙ ማድረግ ነው::

በድርድር ወይም በዕርቅ ያለቀ ጉዳይ ባለጉዳች ተስማምተውበት ወደ ጽሁፍ ተቀይሮ ከተፈራረሙበት ይግባኝ የሌለውና እንደመጨረሻ ውሳኔ ተቆጥሮ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የሚፈጸም ነው::[8] ድርድር ወይም ዕርቅ ከርከር ከተጀመረ በኃላ ወይም ከርከር ሳይጀመር ሊደረግ ይችላል:: ከርከር ከተጀመረ በኃላ እርቅ ከተፈጸመ እርቁ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተረጋግጦ በፍርድ ቤት ተመዝግቦና ጸድቆ ቀጥታ ፍርድ ሆኖ ይፈጸማል::[9] ሆኖም ዕርቁ ወይም ድርድሩ ከፍርድ ቤት ውጭና ከርከር ሳይጀመር የሚደረግ ከሆነ ስምምነቱ እንደውል የሚቆጠር ሆኖ እንደ እርቁ (እንደ ውሉ) ይፈጸምልኝ የሚለው ወገን በፍርድ ቤት ክስ ሊያቀርብ የሚችል ቢሆንም ፍርድ ቤቶች ዕርቁ (ድርድሩ) ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ካልሆነና ባለጉዳዮቹ ካልተካካዱበት በቀጥታ ወደ ፍርድ ቀይረው ሊያስፈጽሙት ይችላሉ::[10]

የግልግል ዳኝነት ማለት ደግሞ ባለጉዳዮች አለመግባባታቸውን በጋራ ስምምነታቸው ለአንድ ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን አቅርበው ማስረጃቸውንና ክርክራቸውን ሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥበት የሙግት መፍቻ ዘዴ ነው::[11] በፍትሐብሔር ሕጉም የግልግል ዳኝነት ተዋዋይ ወገኖች የአንድ ክርክርን ውሳኔ ለአንድ የዘመድ ዳኛ ለሆነው ሶስተኛ ሰው አቅርበው የዘመድ ዳኛው በህግ አግባብ ክርክሩን ተመልክቶ እንዲወስን የሚያደርጉበት ውል መሆኑ ተደንግጓል።[12]

በአጠቃላይ ድርድር፣ ዕርቅና የግልግል ዳኝነት በባህላዊ መንገድ ወይም ዘመናዊ በሆነ ሁኔታና ተቋማት ሊከናውኑ ይችላሉ:: በሀገራችን ከፍትሐብሔር ሕጉ ባሻገር ህገ-መንግስቱም ቢሆን ስለ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች እውቅና ሰጥቷል:: ለምሳሌ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 34(5) የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖት ወይም በባህል ሕጎች መሰረት መዳኘትን ይፈቅዳል:: ከዚህ አንጻር ህገ-መንግስቱን ወይም ሌሎች ሕጎችንና ሞራልን እስካልተቃረኑ ድረስ ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የድርድር፣ የእርቅና የግልግል ዳኝነት አፈታት ዘዴዎች የሚበረታቱና ለተከራካሪዎችም ሆነ ለፍትህ ስርዓቱ ጠቃሚ መሆናቸው ይታመናል::

በገጠር መሬት አለመግባባት ጊዜ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ ወይ? የሕግ ማዕቀፎቹስ ይህን አስመልክቶ ምን ይላሉ? የሚለውን ቀጥለን እንመለከታለን:: የኢፌዴሪ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ የመሬት

---

[6] ብርሀነ አሰፋ፣ ማስታወሻ ቁ. 1፣ ገጽ 31፤ Adriana Herrera & Maria Guglielma da Passano, supra note 3, p.82

[7] የፍ/ሕ/ቁ 3318(1)

[8] የፍ/ሕ/ቁ 3312 እና 3324 እንዲሁም *የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ ኑጋሪት ጋዜጣ፣ 1958 ዓ/ም* (ከዚህ በኃላ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ እየተባለ የሚጠራ) ቁጥር 277 ተጣምረው ሲነበቡ ይህን ሀሳብ ይሰጡናል::

[9] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274 - 277

[10] የፍ/ሕ/ቁ 1731(1)፣ 3312(1)፣ 3324፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 371 እና ተከታይ ድንጋጌዎች፤ ከ284(1) ተጣምረው ሲነበቡ

[11] Adriana Herrera & Maria Guglielma da Passano, supra note 3, p.74

[12] የፍ/ሕ/ቁ 3325 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 317

ይዞታን አስመልክቶ ክርክር ሲነሳ በቅድሚያ ተከራካሪ ወገኖች ክርክሩን በውይይትና በስምምነት እንዲፈቱ ጥረት ይደረጋል፤ በስምምነት መፍታት ካልተቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጡ ሽማግሌዎች አማካይነት በሽምግልና ይታያል፤ ወይም በክልሎች በሚወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሰረት ይወሰናል በማለት ይደነግጋል።[13]

የአብክመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግም ከመሬት ይዞታና ከመጠቀም መብት ጋር በተያያዘ በሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮች ላይ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ቢሆንም በቅድሚያ አለመግባባቱ ወይም ክርክሩ በሽምግልና ታይቶ በእርቅ እንዲፈታ ጥረት መደረግ ያለበት መሆኑን፤ የአስታራቂ ሽማግሌዎች አመራረጥና የእርቁ ድርድር የሚካሄደው የአባባቢውን ባህላዊ ስርዓት መሰረት አድርጐ በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት መሠረት መሆኑን ይደነግጋ።[14] በተመሳሳይ ሁኔታ የዚህ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ከመሬት ይዞታና ከመጠቀም መብት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ማናቸውም ፍትሐብሔር ነክ አለመግባባት በመጀመሪያ ደረጃ በባለጉዳዮች ፈቃድ በስምምነት እንዲፈታ ጥረት መደረግ ያለበት መሆኑን፤ በስምምነት የመፍታቱን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ከየንዑስ ቀበሌው የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የአካባቢ ሽማግሌዎች ሸንጐ በየሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ምርጫ የሚቋቋም መሆኑን፤ የሽማግሌዎቹ አመራረጥና የእርቁ ድርድር አካሄድ በየአካባቢው ባህል መሠረት መፈጸም እንዳለበት እና በባለጉዳዮች ስምምነት ላይ ተመስርቶ የሽማግሌዎች ሸንጐ በፈታው አለመግባባት ላይ አዲስ የፍትሐብሔር ክስም ሆነ ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል መሆኑን ያብራራል።[15]

ስለ ሽማግሌዎች ሸንጎ አሰራር፣ አመራረጥ፣ የስራ ዘመን፣ ተግባርና ኃላፊነት እና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአዋጁና በደንቡ ማስፈጸሚያ መመሪያ ላይ በዝርዝር ተደንግገው እናገኛለን።[16] የአዋጁ፣ የደንቡም ሆነ የመመሪያው ይዘት በአጠቃላይ የገጠር መሬት አለመግባባት ሲከሰት መጀመሪያ በባለጉዳዮች ፈቃድ በስምምነት (በድርድር) እንዲፈቱ ጥረት ይደረጋል።[17] ቀጥሎ ባለጉዳዮች በራሳቸው መፍታት ካልቻሉ በሽማግሌዎች ሸንጎ እንዲታይ ይሆናል። የሽምግሌዎች ሸንጎም ባለጉዳችን ለማስማማት (በእርቅ ወይም ሽምግልና) ይሞክራሉ።[18] ከዚህም አልፎ የሽማግሌዎች ሸንጎ ውሳኔ እንዲሰጡ ባለጉዳዮች ከተስማሙ ማስረጃ አሰባስበው ውሳኔ (የግልግል ዳኝነት) ሊሰጡ ይችላሉ።[19] ስለሆነም የክልላችን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ለድርድር፤ ለዕርቅና የግልግል ዳኝነት ዕውቅና የሰጠ መሆኑንና ከመሬት ጋር የተያያዘ አለመግባባት በተቻለ መጠን በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ እንዲያልቅ ጽኑ ፍላጎት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የሕጉ ይዘት ይህን ሲመስል በተግባር በበርካታ ፍርድ ቤቶች የሚነሳው ጥያቄ የገጠር መሬት ክርክር ሲኖር ባለጉዳች አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን ሳይጠቀሙ ወይም ሳይሞክሩ በቀጥታ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላሉ ወይስ አይችሉም የሚለው ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ የፌደራሉ አዋጅ ከላይ በተገለጸው መልኩ የደነገገ ሆኖ አንዳንድ

[13] *የኢፌዴሪ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997* (ከዚህ በኋላ አዋጅ ቁ. 456/1997 እየተባለ የሚጠራ) ፣ አንቀጽ 12

[14] *የተሻሻለው የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር133/1998* (ከዚህ በኋላ አዋጅ ቁ. 133/1998 እየተባለ የሚጠራ) ፣ አንቀጽ 29

[15] *የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ስርዓትን ለማስፈፀም የወጣ ክልል መስተዳደር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 51/1999* (ከዚህ በኋላ ደንብ ቁጥር 51/1999 እየተባለ የሚጠራ)፣ አንቀጽ 35

[16] የደንብ ቁጥር 51/1999 ማስፈጸሚያ መመሪያ አንቀጽ 48 - 57

[17] ዝኒከማሁ፣ መመሪያ፣ አንቀጽ 48.1.1

[18] ዝኒከማሁ፣ መመሪያ፣ አንቀጽ 48.1.2 እና 48.1.3

[19] ዝኒከማሁ፣ መመሪያ፣ አንቀጽ 57.2 እና 57.4

ክልሎችም የገጠር መሬት አለመግባባት በቀጥታ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ በመከልከል ደንግገዋል::[20] በሌላ በኩል በሌሎች ክልሎች በቅድሚያ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ መጠቀም ግዴታ ሳይሆን በባለጉዳች ስምምነት የተመሰረተ መሆኑን ተደንግጓል::[21] አማራ ክልልን በተመለከተ በአንድ ወቅት በወረዳ ፍርድ ቤቶች ዘንድ የህሳብ ልዩነት በመነሳቱ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የሰጠውን ውሳኔ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል::

> *... ሕጉ ወደ ፍርድ ቤት በቀጥታ መሄድ የለበትም የሚለውን አጠቃቀም ማስቀመጥ ቢፈለግ ኑሮ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ከማቅረቡ በፊት አለመግባባቱን በሽምግልና ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለበት በሚል ያስቀመጠው ነበር:: ከዚህ በተጨማሪም የአዋጁ አንቀጽ 29(2) እና የደንቡ አንቀጽ 35(1) የሚደነገጉት ሽምግልናው በባለጉዳዮች ፈቃድ (ስምምነት) ከሆነ ብቻ መሆኑን ነው:: በመሆኑም ማንኛውም ሰው ጉዳዩን በስምምነት መጨረስ አልፈልግም ወደ ፍርድ ቤት በቀጥታ አቀርባለሁ ቢል መብቱ የተጠበቀ ነው ማለት ነው::... የማስፈጸሚያ መመሪያው አንቀጽ 48 - 57 ያሉት ድንጋጌዎችም የሚያሳዩን በቅድሚያ በባለጉዳች ስምምነት፤ ካልሆነ የሽማግሌዎች ሸንጎ ሊያስማማቸው እንደሚችልና... ባለጉዳች ይህን ካልመረጡ ግን በቀጥታ ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን መውሰድ የማይከለከሉ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል*[22] በማለት ወስኗል::

በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እምነት ይህ ውሳኔ ተገቢውን የሕግ ትርጉም የተከተለ ነው:: በአንድ በኩል ከፌደራሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12 ይዘት በመሬት ክርክር አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴን መጠቀም በባለጉዳዮች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንጂ በቅድሚያ መሞከር ግዴታ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል:: ይህን አዋጅ ተከትሎ የወጣው የአብክመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ የማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 51/1999 እና መመሪያውም ይዘት ይህን የተከተለ ሆኖ እናገኘዋለን:: የፌደራሉን አዋጅ የተከተለ ሕግ መውጣቱም ተገቢም ነው::[23] ከዚህ አንጻር ከፌደራሉ ገጠር መሬት አዋጅ ሀሳብ ውጭ ባለጉዳዮች በቀጥታ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ አይችሉም ብሎ መደንገግ ተገቢ አይደለም:: በሌላ በኩል የክልላችን የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ 29፣ ደንቡ አንቀጽ 35 እና መመሪያ አንቀጽ 48 - 57 ያሉት ድንጋጌዎች አንድ በአንድ ሲታዩ ወደ ፍርድ ቤት በቀጥታ በመሄድ ክስ የማቅረብ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ

---

[20]ለምሳሌ *በተሻሻለዉ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999*፣ አንቀጽ 16(1) መሰረት በድሚያ አቤቱታው ለቀበሌው አስተዳደር ይቀርባል፤ ተከራካሪ ወገኖች ሁለት አስታራቂ ሽማግሌዎችን ይመርጣሉ፤ ሰብሳቢው በተከራካሪ ወገኖች ወይም በሁለቱ አስታራቂ ሽማግሌዎች ይመረጣል:: የተመረጡት አስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔያቸውን በ15 ቀናት ውስጥ ለቀበሌው አስተዳደር ማሳወቅ አለባቸው:: በአስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል:: እንዲሁም *የተሻሻለዉ የደቡብ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999*፣ አንቀጽ 12 ከኦሮሚያ ክልል ሕግ ጋር ተመሳሳይ ይዘት አለው።

[21]ለምሳሌ *የተሻሻለዉ የትግራይ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር136/2000*፣ አንቀጽ 28(1) መሠረት ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ክርክሩን በስምምነት እንዲፈቱ ጥረት ይደረጋል:: ይህም ካልተቻለ በሽማግሌዎች ወይም በእርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ:: ነገር ግን ከላይ በተገለፀው መልኩ ክርክሩን መፍታት ካልተቻለ ጉዳዩ ለቀበሌው የገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴ ቀርቦ ውሳኔ ያገኛል::

[22]የሰከላ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ዘመኑ ይርዴ፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 48849፣ መጋቢት 10/2004 ዓ/ም

[23]ምክንያቱም መሬትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና ጥበቃን በተመለከተ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የፌደራል መንግስት እንደሆነ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51(5) ሥር ተደንግጓል:: የዚሁ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52(2)(መ) ደግሞ ክልሎች የፌደራሉ መንግስት የሚያወጣውን ሕግ መሠረት አድርገው መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን የማሥተዳደር ሥልጣን እንዳላቸው ይደነግጋል:: በሌላ መልኩ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50(9) የፌደራል መንግስቱ በአንቀፅ 51 ከተሠጡት ሥልጣንና ተግባሮች መካከል እንደ አስፈላጊነቱ ለክልሎች በውክልና ሊሠጥ እንደሚችል ደንግጓል:: የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997ን ያወጀ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(1) መሰረት ክልሎች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚስፈልጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሕግ እንዲያወጡ ውክልና ሰጥቷል። ከዚህ አንጻር በክልል ደረጃ የሚወጣ ሕግ የፌደራሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የሚደነግጋቸውን መሰረታዊ መርሆዎች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት።

ባለጉዳዮች አለመግባባታቸውን መጀመሪያ በራሳቸው ጥረት (በድርድር)፣ ይህ ካልሆነ በሽምግልና ወይም በዕርቅ (በሽማግሌዎች ሸንጎ አስማሚነት)፣ ከዚህም አልፎ በሽማግሌዎች ሸንጎ እንዲወሰንላቸው ከተስማሙ በግልግል ዳኝነት አይነት እንዲወሰን በማድረግ እልባት ሊያገኙ የሚችሉ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ባለጉዳዮች የአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን ጥቅም በመረዳት የገጠር መሬት አለመግባባትን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለህግና ለሞራል ሳይቃረኑ እንዲፈቱ ጥረት መደረግ አለበት ሲባል ሰዎች ይህን አውቀው እንዲጠቀሙበት ግንዛቤ መፈጠር አለበት ለማለት እንጂ በቀጥታ ፍርድ ቤት ማቅረብ አይቻልም ለማለት አይደለም፡፡

### 1.2 በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚደረጉ ክርክሮች

ከገጠር መሬት ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ምን እንደሚመስል ከላይ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ከአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ውጭ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሌሎች በሕግ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ፊት የሚደረገውን የክርክር አፈታት ዘዴ እንመለከታለን፡፡

የገጠር መሬት ይዞታ ዋስትና ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች አንዱ ፍትህ የማግኘት መብት ነው፡፡[24] የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መብት ጥበቃ በሕግ በበቂ ደረጃ ተደንግጓል ቢባል እንኳ መብቶቹ በሚጣሱበት ጊዜ አጥፊዎችን ለማረምና መብቱን ለማስከበር እንዲቻል ለማድረግ ፍትህ የማግኘት መብት ከሌለ የሕጉን ድንጋጌ ትርጉም አልባ ያደርገዋል፡፡ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት አለው።[25] በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ ወይም ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በቀር በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ የፍትሐብሔር ክርክሮችን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ነው፡፡[26] የገጠር መሬት ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚችል (Justiciable Matter) ስለሆነ በህገ መንግስቱ በተደነገገው አግባብ በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው አካል በኩል ቀርቦ እልባት ሊያገኝ የሚችል ነው፡፡

በአለም ላይ በብዙ ሀገሮች ከመሬት ጋር የተያያዙ ክርክሮች የሚፈቱት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቢሆንም አንዳንድ ሀገሮች ልዩ የመሬት ክርክሮችን የሚያዩ ችሎቶች ወይም ፍርድ ቤቶች (land courts) ያቋቁማሉ፡፡[27] በሀገራችን በንጉሱ ዘመን አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ እንደተጠበቀ ሆኖ የመሬት ክርክር የሚታየው በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ነበር፡፡[28] በደርግ ዘመን የመሬት ክርክር በመደበኛ ፍርድ ቤት መሆኑ ቀርቶ በገበሬዎች ማህበር ፍርድ ሸንጎ እንዲታይ ተደርጓል፡፡[29] የገበሬ ማህበራትን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ መሰረት የገጠር መሬት ክርክር በቀበሌ፣ በወረዳና በአውራጃ ደረጃ በተቋቋሙ ፍርድ ሸንጎዎች ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ይግባኝ የሚታይ ነበር፡፡[30] ስለሆነም በደርግ ዘመን በማንኛውም ሁኔታ የገጠር መሬት ክርክር ለመደበኛ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ተደርጎ የነበረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

---

[24] በሪሁን አዱኛ ምህረቱ፣ *የገጠርና የከተማ መሬትን የሚመለከቱ ህጐችና አፈጻጸማቸው በኢትዮጵያ* ፡ በፌዴራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም የተዘጋጀ (የካቲት 2004 ዓ/ም፣ ያልታተመ)፣ ገጽ 81

[25] የኢፌዲሪ ህገ መንግስት፣ 1987 ዓ/ም፣ አንቀጽ 37(1)

[26] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 4

[27] Bengt Andersson, future Framework of Land Related Laws in Amhara National Regional State: Sida Amhara Rural Development Programme, (July 2005), p. 96

[28] *የገጠር መሬትን የህዝብ ሀብት ለማድረግ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 31/1967 ዓ/ም፣* አንቀጽ 28(1) ላይ አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚገኙ የገጠር መሬት ክርክሮች በሙሉ የተሰረዙ መሆኑን ስለሚደነግግ ነው፡፡

[29] አዋጅ ቁ. 31/1967፣ አንቀጽ 28 (2) (3) እና *የገበሬ ማህበራትን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 223/1974 ዓ/ም*

[30] አዋጅ ቁጥር 223/1974፣ አንቀጽ 36 - 40 እና ከአንቀጽ 53 - 60

በአሁኑ ወቅት የገጠር መሬትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ በቅድሚያ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል፡፡ ይኸውም በቅድሚያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና ስምምነት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል፡፡ በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጡ ሸማግሌዎች ወይም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በሚደነገገው መሰረት ይወሰናል፡፡[31] ከዚህ የምንረዳው ጉዳዩ በአማራጭ የሙግት መፈቻ ዘዴዎች የማይቋጭ ከሆነ መደበኛ በሆነ ሁኔታ ክርክሩ በየት በኩልና በምን አይነት ተቋም ይቋጫል የሚለው ለክልል መንግስታት የገጠር መሬት ሕጎች የተተወ መሆኑን ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ክልሎች ባወጧቸው ሕጎች ክርክሩ የሚጀምርበት ተቋም የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ በትግራይ ክልል በስምምነት ወይም በሸማግሌ ተሞክሮ ካልተሳካ ክርክሩ የሚቀርበው ለቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴ ነው፡፡[32] የደቡብና የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አዋጆች ደግሞ በቀበሌ መሬት አስተዳደር በኩል ክርክሩ ለሸማግሌዎች ቀርቦ እንደሚወሰን ይደነግጋሉ፡፡[33] በእነዚህ ሶስት ክልሎች የገጠር መሬት አዋጆች መሰረት በቀበሌ አስተዳደር በኩል ለሸማግሌዎች ቀርቦ በተወሰነው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የይግባኝ ቀጥሎም የሰበር አቤቱታዎች እንደሁኔታው ለቀጣዮቹ ፍርድ ቤቶች የሚያቀርብ መሆኑን መረዳት ይችላል፡፡

በአማራ ክልል ቀደም ሲል የመሬት ክርክር እልባት እንዲያገኝ የሚጀምረው በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች (social courts) ነበር፡፡[34] ከጊዜ በኃላ ግን ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ተሰጥቶ የነበረው የገጠር መሬት ክርክር በተሻሻለው የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ተነስቶ በመደበኛ ፍርድ ቤት (ወረዳ ፍርድ ቤት) እንዲጀምር ተደርጓል፡፡[35]

ከዚህ አንፃር በክልላችን የገጠር መሬት አለመግባባት በባለጉዳዮች ፈቃድ በስምምነት ወይም በሸማግሌዎች ሽንጎ እልባት የማያገኝ ከሆነ ወይም ባለጉዳዮች እነዚህን አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ለመጠቀም ካልመረጡ ክርክሩ በመደበኛ ወረዳ ፍርድ ቤቶች ይጀምራል፡፡ ይኸውም አሁን ባለው የሕግ ማዕቀፍ መሬት በዋጋ የማይተመን ሀብት በመሆኑ የወረዳ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡[36] በመቀጠልም ክርክሮቹ እንደሌሎች የፍትሐ ብሔር ክርክሮች በይግባኝ (መጨረሻም በሰበር) ለቀጣዮቹ የክልሉ ፍርድ ቤቶች እርከኖች ብሎም እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይደርሳሉ፡፡

### 1.3 የአስተዳደር አካላት ተሳትፎ እና አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች

በዚህ ክፍል የገጠር መሬት አለመግባባትን በመፍታት ረገድ የመሬት አስተዳደር ተቋማትን ተሳትፎና አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ስለሚችሉ ጉዳዩች እንመለከታለን፡፡

በክልላችን በገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ሕጎች ላይ የገጠር መሬትን ከመለካት፣ ከመመዝገብ እና መረጃን ከመያዝ ጋር የተያያዙ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካላት ግዴታዎች እና ሀላፊነቶች በሰፊው ተዘርዝረዋል፡፡[37] ከእነዚህ

[31] አዋጅ ቁጥር 456/1997፣ አንቀፅ 12
[32] አዋጅ ቁጥር 136/2000፣ አንቀፅ 28
[33] አዋጅ ቁጥር 110/0999፣ አንቀፅ 12 እና አዋጀ ቁ. 130/1999፣ አንቀፅ 16(1) በቅድም ተከተል
[34] የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 20/1989 ዓ/ም ፣አንቀፅ 14
[35]የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 148/1999 ዓ/ም፣ በአዋጅ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው ክርክሮቹ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች እንዳይደረጉ የሆነበት ምክንያት የገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች በመፈታትና ፍትሐ ብሔር ነክ ክርክሮችን በመዳኘት ረገድ ከሌሎች ሕጎች ጋር ለማጣጣም በማሰፈለጉ ነው፡፡
[36]የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 18 እና በአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ/ም፣ አንቀፅ 7 (1)
[37]አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 22 - 27 እና ደንብ ቁጥር 51/1999፣ ከአንቀጽ 19 - 21

በርካታ ግዴታዎች ውስጥ ከገጠር መሬት አለመግባባት ጋር የሚያያዘው መሬትን በተገቢው መንገድ መጠኑን/ስፋቱን፣ አዋሳኙንና ልዩ ምልክቱን በመለየት መዝግቦ መያዝና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መስጠት አንዱ ነው።[38] የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶ የተሰጠው ሰው ተቃራኒ የፅሑፍ ማሰረጃ ካልቀረበ በስተቀር የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል።[39] ይህ ማለት የመሬት ባለይዞታ እንጂ ባለሀብት የማይባል መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በፍ/ሕ/ቁ 1195 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የማይቀሳቀስ ንብረት ባለቤት እንደሆነ ያስቆጥረዋል ከሚለው ሕግ ጋር የሚዛመድ ነው። የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት የሆነ ሰው ተገቢው የባላሀብትነት የምስክር ወረቀት ከተሰጠው ማናቸውንም የሚነሳበትን ክርክር ለማስረዳት ቀላል እንደሚሆንለት ሁሉ (በፍ/ሕ/ቁ 1196 መሰረት ተቃራኒ ማሰረጃ ቀርቦ ካልተሰረዘበት በቀር) የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠው ሰው እንዲሁም ተቃራኒ ማሰረጃ ካልቀረበበት በስተቀር በይዞታው ላይ የሚነሳውን ማናቸውንም ክርክር ለመርታት ይቀለዋል።

ከዚህም ባለፈ በአጠቃላይ የገጠር መሬት በማን ይዞታ ስር እንደሚገኝ፣ ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን፣ ደረጃው ምን አይነት እንደሆነ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውልና ባለይዞታው ምን መብትና ግዴታዎች እንዳሉበት የሚገልጽ መረጃ ተመዝግቦ አግባብ ባለው አካል እንደሚያዝ አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 6(5) ይገልፃል። በሊዝ ወይም በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬትም አግባብ ባለው አካል መመዝገብ እንዳበት የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6(6) ያሳያል። ስለሆነም ከዚህ አዋጅ እንደምንረዳው የገጠር መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ለመሆን (ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፍም) መመዝገብ ያለበት መሆኑን ነው። ለምሳሌ አንቀጽ 8(2) የገጠር መሬት ኪራይ ውል አግባብ ባለው አካል ጸድቆ መመዝገብ ያለበት መሆኑን ይገልፃል።

በዚህ መሠረት ክልሎች የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብት የሚተላለፍበትን ፎርም በእየራሳቸው እንዲስቀምጡ ይጠበቃል። የአማራ ክልል አዋጅ ማንኛውም የመሬት ስጦታ ስምምነት በፅሑፍ መደረግ ያለበት መሆኑን እና መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ባለው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት መመዝገብ ያለበት መሆኑን አንቀጽ 17(5)(6) ይደነግጋል። እንዲሁም ከ3 ዓመት በላይ የሚደረግ የመሬት ኪራይ ውል በፅሑፍ መደረግ ያለበት መሆኑንና መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ያለበት መሆኑን አንቀጽ 18(2)(5) ደንግጓል። በተጨማሪም ከመሬት ጋር የተያያዘ ማንኛውም መብትና ግዴታን የሚመለከት ተግባር በጽ/ቤቱ ካልተመዘገበ በስተቀር በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችል አንቀጽ 23(4) ይደነግጋል።

እነዚህ ሁሉ የመሬት ይዞታ ማሰረጃ ሰነዶች በአስተዳደሩ ተመዝግበው የሚገኙ ከሆነ ከገጠር መሬት ባለይዞታነትና ከመጠቀም መብት ጋር የተያያዙ እንደ የመሬት ለውጥን፣ ኪራይን፣ ስጦታን፣ ድንበር መግፋትና ውርስን ወዘተ የተመለከቱ ክርክሮች በቀረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካሉን ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል ማስረጃ መጠየቃቸው የማይቀር ነው። በዚህ ረገድ የሚመለከተው ጽ/ቤት ግዴታውን በመወጣቱ በአግባቡ የተቀመጠ ሰነድ ካለ ክርክሮችን ለመፍታት ጠቃሚ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካላት ተግባራቸውን በተገቢው መንገድ ከተወጡና

[38]አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 24 እና ደንብ ቁጥር 51/1999፣ አንቀጽ 20፤ በአዋጅ ቁጥር 456/97፣ አንቀጽ 6(3) ላይም ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ አግባብ ባለው ባለስልጣን የሚዘጋጅና የመሬቱን ይዞታ ስፋት፣ አጠቃቀምና ሽፋን፣ የለምነት ደረጃና አዋሳኞቹን እንዲሁም ሀላፊነትና ግዴታን የያዘ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንደሚኖረው ይደነግጋል።

[39] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀፅ 24(4)፤ ደንብ ቁጥር 51/1999፣ አንቀጽ 20(4)

ትክክለኛ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከሰጡ፣ መመዝገብ ያለበትን የመሬት ክንውን በአግባቡ ከመዘገቡ የገጠር መሬት አለመግባባትን ለመፍታት የበኩላቸውን ሚና ተወጥተዋል ማለት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተገለፀው መልኩ የአስተዳደር አካላት ግዴታዎችን ለመወጣት የገጠር መሬትን በተመለከተ (ስለ እያንዳንዱ መሬት) ሙሉ መረጃ ይኖራቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ በፍርድ ቤት በተያዙ የገጠር መሬት ክርክሮች ላይ ማስረጃዎችን እንዲልኩ በፍርድ ቤት ሊታዘዙ ይችላሉ፡፡[40] አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል ባለሙያዎች ቦታው ድረስ ሂደው የሚመለከታቸውን አካላት ይዘው አጣርተው እንዲያመጡ ሊያዝ ይችላል፡፡[41] እነዚህ ትዕዛዞች በሚሰጡበት ጊዜ የአስተዳደር አካሉ ወይም ባለሙያዎች የሚሰጡት ማስረጃ የገጠር መሬት ክርክርን በተገቢው መንገድ ለመፈታት ሚናው የጎላ ነው፡፡ በአንፃሩ የአስተዳደር አካሉ ተገቢውን ማሰረጃና የማጣራት ውጤት ካልሰጠ የክርክሩ ውጤት በዚያው ልክ ያማረና የተቀላጠፈ ላይሆን ይችላል፡፡

ሰለሆነም የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካላት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በተያዙ ክርክሮች ላይ ክርክሮቹን ፈጣን፣ ውጭ ቆጣቢና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለመቋጨት ሚናቸውና ተሳትፏቸው የጎላ መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል፡፡ በእርግጥ በተግባር ሲታይ ማስረጃዎችን አጥርቶ በመያዝ ወይም በመመዝገብ እንዲሁም የገጠር መሬትን በማስተዳደር ረገድ የአስተዳደር አካሉ በርካታ ችግሮች ያሉበትና ግዴታውን በተገቢው መንገድ እየተወጣ አለመሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ።[42] በተግባርም እንደሚታወቀው በአንድ መሬት ላይ ሁለትና ከዚያ በላይ ደብተር የመስጠት፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሲሰጥም አዋሳኞችን በአግባቡ አለመግለጽ፣ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር ቦታው ድረስ ሄዶ አለማየት፣ በይዞታ ላይ የተጠቀሰው አዋሳኝ በእርግጥ በተጨባጭ ከመሬቱ ላይ ከሚገኘው ጋር ያለመጣጣም፣ የመሬት ልኬታው የመሬቱን መጠን በትክክል አለማስቀመጥ፣ የተለያዩ ማስረጃዎችን የመስጠት፣ የመሬት ድልድል በተካሄደበት ወቅት መሬቱ የተመዘገበበት የገጠር መሬት መመዝገቢያ መዝገብ መጥፋት እና ሌሎች የመሳሰሉት ችግሮች ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የአስተዳደር አካሉ አቅሙን በማጠናከር ያሉበትን ችግሮች በመቅረፍ የተጣሉበትን ግዴታዎች ሊወጣ ይገበዋል።

በሌላ በኩል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካላት በአንዳንድ ጉዳዩች ላይ በራሳቸው የሚሰጧቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ክርክሮችን ሊቀንሱ ይችላሉ፡፡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የሚሰጡት ብዙ ጊዜ የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታዎች ሳይውጡ ሲቀሩ ነው፡፡

በፌደራልም ሆነ በክልላችን የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ውስጥ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች ግዴታዎች ተደንግገዋል፡፡[43] እነዚህም በይዞታም ሆነ በኪራይ የያዘውን መሬት የመንከባከብ፣ መሬቱ አከባቢ ዛፍ መትከልና ተንከባክቦ ማሳደግ፣ በአስተራረስ ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ፣ በመሬቱ አካባቢ የሚገኙ የዱር እንስሳትና አዕዋፎች እንዳይጎዱ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ፤ ወሰናቸው የተከለለ መሬቶችን ድንበር ያለመጋፋትና ተለይተው የሚታወቁ መንገዶችን ያለመዝጋት እና ሌሎች የመሳሰሉት ግዴታዎች ናቸው፡፡

---

[40] ይህም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሰረት ተከራካሪዎች እንዲቀርብላቸው ሲጠይቁ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው እንዲቀርብ ሊያዘው የሚችለው ነው፡፡

[41] ይህ ደግሞ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 132 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ምትክ ዳኛ እንደመሾም ወይም የልዩ አዋቂ አስተያየትና ማጣሪያ ከመጠየቅ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

[42] ደሴ ስዩም፣ *የገጠር መሬት ህግጋትና ኢያጋጠሙ ያሉ ችግሮች፣* ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች የተዘጋጀ የስልጠና ጽሑፍ፣ ባህርዳር ዩንቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲቱት፣ (መስከረም/2006 ዓ/ም)፣ ገፅ 44 - 53

[43] አዋጅ ቁጥር 456/1997፣ አንቀፅ 10 እና 13፣ አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 20

እነዚህን ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ የሆነ ሰው የፍትሐ ብሔር እና የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች (administrative measures) ይወሰዱበታል፡፡ በመጀመሪያ እንደቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡[44] በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ስህተቱን ሊያርም ያልቻለ እንደሆነ ከተሰጠው የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለይዞታው በራሱ ድክመት መሬቱን ባለመንከባከቡ ምክንያት በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ የመጠቀም መብቱን መሬቱን ለመንከባከብ ግዴታ ለሚገባ ሌላ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በኪራይ እንዲሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በላይ የተቀመጠው አስተዳደራዊ እርምጃ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ በመሬት የመጠቀም መብቱን ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ የማፈናቀያ ካሳ ተከፍሎት መሬቱን እንዲለቅ እስከ መገደድ የሚደርስ እርምጃ ይወሰዳል፡፡[45]

በተጨማሪም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መስጠትና ደብተሩ የተሰጠው በተለያዩ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መሰረዝ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚስጥበት ተግባር ነው፡፡[46]

አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ከቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊዘልቅ ይችላል።[47] በቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው በተሰጠ በ15 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሊያመለክት ይችላል። የወረዳ ጽ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በደረሰው በሰላሣ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለወረዳ ፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይችላል። የወረዳ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንደተገቢነቱ ይግባኙን ወይም የሰበር አቤቱታውን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ማለትም የወረዳ ፍርድ ቤቱ የጽ/ቤቱን ውሳኔ ከሻረው የተሻረበት ወገን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚጠይቅ ሲሆን ካጸናው ግን ሁለተኛ ይግባኝ ስለማይቻል ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርበው በሰበር ይሆናል ማለት ነው።

ይህ የሚያሳየው በሌሎች የአስተዳደር አካለት ውሳኔ በይግባኝ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ቀርቦ የሚታይበት የሕግ ማዕቀፍ ካለመኖሩ አንፃር ሲናፃፀር የገጠር መሬትን አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፍርድ ቤት በይግባኝ ማየት (review of administrative decisions) መቻሉ የተሸለ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያጎናፅፍ መሆኑን ነው፡፡[48]

### 1.4 በገጠር መሬት የይዞታ ክርክር ወቅት ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች

በፍርድ ቤት ክርክር የሚደረግባቸው ጉዳዮች ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ናቸው፡፡ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የተፈለጉ ጭብጦች ሕግን የሚመለከቱ ቢሆኑ እንኳ ወደ ሕግ ጭብጥነት ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ፍሬ ነገሮችን የሚመለከቱት ጭብጦች የሚረጋገጡት ወይም የሚስተባበሉት በማስረጃ አማካኝነት

---

[44] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 21(1)

[45] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 21(2)፣

[46]የፍ/ሕ/ቁ 1195 እና 1196ን ማየት ጠቃሚ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም *ወ/ሮ ጽጌ ኦጥናፌ እና ባላምባራስ ውብ ሸበሸ* በተከራከሩበት ጉዳይ *(ቅጽ 3) መ/ቁ 14554፣ ታህሳስ 20/1998 ዓ/ም*፣ የምስክር ወረቀት መሰረዝ የፍርድ ቤት ስልጣን አለመሆኑን ወስኗል፡፡

[47] ደንብ ቁጥር 51/99፣ አንቀፅ 36

[48]ለምሳሌ በፍ/ሕ/ቁ 1196 መሰረት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሰው አስተዳደራዊ እርከኑን ተከትሎ ቅሬታ ከሚያቀርብ በስተቀር ይግባኝ የሚልበት ስርዓት የለም፡፡ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰረዘበት ሰው ግን ሊሰረዝ አይገባም የሚልበት ምክንያት ካለው ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል ማለት ነው፡፡

ነው።።[49] የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ/ለማስተባበል ከሚቻልባቸው ዘዴዎች እና ማስረዳት ከሚፈለገው ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ ጋር ማስረጃው የሚኖረውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ ማስረጃን በተለያዩ መንገዶች ከፍሎ ማየት ይቻላል።።[50] ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ከምንጠቀምበት ዘዴ አንፃር ማስረጃዎች የቃል ማስረጃ (oral evidence)፣ የሰነድ ማስረጃ (documentary evidence) እና የቁሳዊ ወይም ገላጭ ማስረጃ (real or demonstrative evidence) ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ። በማስረጃነት የሚገለፀው ፍሬ ነገር ሊያስረዳው ከተፈለገው ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ደግሞ ማስረጃን ቀጥተኛ ማስረጃ (direct evidence) እና ቀጥተኛ ያልሆነ ወይም የአከባቢ ማስረጃ (indirect or circumstancial evidence) ብሎ መከፋፈል ይቻላል።።

*የቃል ማስረጃ* የሚባለው ምስክር የሆነ ሰው በፍርድ ቤት ቀርቦ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በስሜት ህዋሳቱ የተረዳውን የሚናገርበት ሁኔታ ነው።። *የጽሁፍ (የሰነድ) ማስረጃ* የሚባለው ደግሞ ማንኛውም በውስጡ ወይም በላዩ ላይ በፊደል፣ በአሀዝ፣ በምልክት ወይም በሌላ የሀሳብ መግለጫ ነገር የተቀረጸበት፣ የተጻፈበት ወይም የተሳለበት ነገርን የሚመለከት ነው። የሰነድ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገኖች ወደ ክርክሩ ከመግባታቸው በፊት ሰነዱ አስቀድሞ የነበረ ከሆነና ይህ አስቀድሞ የነበረ ሰነድ አሁን በፍርድ ቤት የሚያከራክረውን ፍሬ ነገር መኖር/አለመኖር እውነት/ሀሰት መሆን በራሱ የሚያስነብበው (የሚናገረው) የሚያስተላልፈው መልክት ካለ ነው።። እንደዚህ አይነት ሰነዶች ሁለት አይነት ናቸው። በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ግለሰቦች የተዘጋጁ የግል ሰነዶች (private documents) ለምሳሌ ውል፣ ዕርቅ፣ የግል ጽሁፍ ወዘተ ወይም በህዝባዊ/መንግስት ተቋማት በሰራተኛ፣ በሹም ወዘተ የተዘጋጁ፣ የተረጋገጡና በእነዚህ አካላት ዘንድ የሚገኙ (public documents) ለምሳሌ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር፣ የስጦታ ወይም የመሬት ኪራይ የተመዘገበበት ሰነድን ያጠቃልላል።

*ቁሳዊ ማስረጃ* ደግሞ ዳኞች በራሳቸው የስሜት ህዋሳት በመጠቀም ስለሚመረምረው ነገር ግልጽ የሚሆንበት የማስጃ አይነት ነው። ለምሳሌ ክርክር የተነሳበት መሬት ሰብል የተዘራ መሆን አለመሆኑን፣ ቤት የተሰራበት መሆን አለመሆኑን ወዘተ በዳኞች በራሰቸው ወይም በምትክ ዳኛ የሚታይና የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር ነው።።

*ቀጥተኛ ማስረጃ* በጭብጥነት በተያዘው ፍሬ ነገር በቀጥታ የሚያስረዳ ሲሆን ለምሳሌ ምስክሩ ቀርቦ በ1989 ዓ/ም ደልዳይ ሆኘ አከራካሪውን መሬት ለእከሌ ሰጥቻለሁ ብሎ ቢመሰክር፣ ደልዳዮች በወቅቱ የተፈራረሙት ሰነድ ቢገኝ፣ በአግባቡ የተዘጋጀ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ቢቀርብ ወይም ዳኛው/ምትክ ዳኛው ቦታው ድረስ ሂዶ ቢለካ እነዚህ ሁሉ ቀጥተኛ የቃል፣ የሰነድ እና የገላጭ ማስረጃዎች ናቸው።።

*ቀጥተኛ ያልሆነ ወይም የአከባቢ ማስረጃ* ጭብጥን ሳይሆን በጭብጥነት ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ግንኙነት ያለውን (አግባብነት ያለውን) ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ በተመለከተ የሚቀርብ የማስረጃ አይነት ነው። ለምሳሌ የተያዘው ጭብጥ ክርክር የተነሳበት መሬት በ1989 ዓ/ም ለከሳሽ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም የሚል ቢሆን እና ምስክሩ የመሰከረው በ1989

[49]በእርግጥ የክርክር ሂደቱ ሁል ጊዜ ማስረጃ እና ማስረጃ ብቻ በመጠቀም ላይፈታ ይችላል።። ይልቁንስ የእምነት ቃል (formal admission)፣ የዳኞች ግንዛቤ (judicial notice) እና ተረጋጋጭ ፍሬ ነገሮች (presumed facts or presumptions) በመጠቀም ሊሆን ይችላል።

[50]ከፍፍሉና አጠቃላይ የሆኑት የማስረጃ መርሆዎች የተወሰዱት Molla Ababu & Worku Yaze, Materials on Law of Evidence: *Notes, Cases, and Questions, Bahir Dar & Jimma Universities* (2010) ከሚለው መጽሐፍ ነው።

ዓ/ም ለከሳሽ ይሰጠው አይሰጠው አላውቅም፤ ሆኖም የተሰጠኝ ነው በማለት ከሳሽ ሲጠቀምበት እና ለሌላ ሰውም ሲያከራየው አውቃለሁ የሚል ቢሆን ለተያዘው ጭብጥ አካባቢያዊ ማስረጃ ነው።

በዋናነት ማስረጃ የሚቀርበው በክሱ መስማት ወቅት ተለይተው የተያዙ የፍሬ ነገር ጭብጦች እውነት ወይም ሀሰት መሆኑን፣ መኖር ወይም አለመኖር፣ እውነታው ከሳሽ የሚለው ወይስ ተከሳሽ የሚለው ስለመሆኑ እና የመሳሰሉትን ለማጣራትና በተቻለ መጠን እውነታው ላይ ለመድረስ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ዳኞች ጭብጥ መያዝ አለባቸው። "በማስረጃ የሚረጋገጠውን ነገር ሳያውቁ ማስረጃን መቀበል በድቅድቅ ጨለማ ያለ ምንም አቅጣጫ ጠቋሚ ነገር እንደመጓዝ ሊቆጠር የሚችል ነው፡፡"[51] በማስረጃ እንዲረጋገጥ የተፈለገው ነገር (object of proof) በግልጽ ከታወቀ በመቀጠል ያን ሊያረጋግጥ የሚችለውን ማስረጃ (evidence) ይሁን ሌላ የማረጋገጫ አይነት /ዘዴ/ መለየት አይከብድም፡፡ ተከራካሪዎች አለን የሚሉትን ማስረጃ ከአቤቱታቸው ጋር አያይዘው ስለሚያቀርቡ ፍርድ ቤቱ የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን ምን ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት ለማዘዝ ይመቸዋል፡፡

የፍሬ ነገርን መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የተፈለገው ማስረጃ በዘፈቀደ ወይም ማስረጃ አቅራቢው ስለፈለገ ብቻ ይቀርባል ማለት አይደለም፡፡ ማስረጃው ሊቀርብ የሚችለው ተቀባይነት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ማንኛውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው ያስረዳዋል ለተባለው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ እና ማስረጃው እንዳይቀርብ በሕግ ያልተከለከለ ሲሆን ነው፡፡

የገጠር መሬት ክርክር የሚያጠነጥንባቸው ፍሬ ነገሮች በአብዛኛው ክርክር የተነሳበት መሬት ለማን እንደተሰጠ ወይም ቀደም ሲል በማን ይዞታ ስር እንደቆየ፤ የመሬቱ መጠን (ስፋት) ፣ አዋሳኝ፣ በ1996/97 ዓ/ም በማን እንደተመዘገበ፣ ተከራካሪዎች መሬት የተሻሻጡ መሆን አለመሆኑ፣ ኪራይ፣ ስጦታ፣ ለእኩል አራሽነት የተሰጠ መሆን አለመሆን፣ ባል ወይም ሚስት ከመጋባታቸው በፊት አንዱ ብቻውን የተመራው መሆን አለመሆኑ፣ ከፍች በኋላ የየድርሻቸውን የወሰዱ መሆን አለመሆኑ፣ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሚች የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆኑ የሚሉ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡[52]

ለገጠር መሬት ይዞታ ክርክር ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ የለም። በአብዛኛው በገጠር መሬት ክርክር ሊቀርቡ የሚችሉት የቃል፣ የሰነድ፣ ገላጭ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ልክ እንደብድር ውል ከ500ብር በላይ በጽሁፍ ወይም በመሀላ ቃል ካልሆነ ማስረዳት አይቻልም እንደተባለው ክልከላ እስከሌለ ድረስ አግባብነት አለው ተብሎ የሚታመን ማስረጃ ሁሉ በገጠር መሬት ክርክር ሊቀርብ ይችላል፡፡ በእርግጥ እንደ ልዩ ሁኔታ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች ይኖራሉ። ይኸውም ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቱ ግዴታዎች መካከል አንዱ መሬትን በአግባቡ መዝግቦ መያዝና ለባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መስጠት እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ የተሰጠው ሰው ተቃራኒ የፅሑፍ ማስረጃ ካልቀረበበት በስተቀር የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል።[53] ይህ የሕግ ግምት ከተወሰደ የገጠር መሬትን ይዞታ አስመልክቶ በፍርድ ቤት ክርክር በሚደረግበት ጊዜ ለምሳሌ ክርክር የተነሳበት መሬት ባለይዞታ ማን ነው

[51]ወርቁ ያዜ ወዳጅ፣ *በገጠር መሬት የይዞታ ክርክር ሂደት ትኩረት የሚያሻቸው የማስረጃ ሕግ ጉዳዮች*፣ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት እና የስዊድን የልማት ተራድኦ ድርጅት ድጋፍ ለወረዳ ፍ/ቤት ዳኞች ስልጠና የተዘጋጀ (ያልታተመ፣ መስከረም 2006 ዓ/ም)፣ ገፅ 32

[52] ፀሐፊው በሥራው ኢጋጣሚ የሚያውቃቸው ናቸው፡፡

[53]አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀጽ 24(4) ፣ በእርግጥ ደንብ ቁጥር 51/1999፣ አንቀጽ 20(4) ተቃራኒ ማስረጃ ነው የሚለው። አዋጁ ተቃራኒ የፅሁፍ ማስረጃ እያለ ደንቡ ይህን አለመከተሉ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል።

የሚለውን ነጥብ ለማስረዳት በፍርድ ቤት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የሰነድ ማስረጃ (የይዞታ መረጋገጫ ደብተር) እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በሌላ በኩል የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው መሬቱን በሕጉ ለተፈቀደለት ሰው በስጦታ ሲያስተላልፍ በወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት መመዝገብ ያለበት መሆኑ ተደንግጓል።[54] በተመሳሳይ ሁኔታ ከሶስት አመት በላይ የሆነ የመሬት ኪራይ ውል በጽ/ቤቱ መመዝገብ ይኖርበታል።[55] ከዚህ አንጻር የስጦታ ውል አለ ወይስ የለም፣ ከሶስት አመት በላይ (ለምሳሌ ለ10 አመት) የተደረገ የመሬት ኪራይ ውል አለ ወይስ የለም የሚሉ ክርክሮች ቢነሱ የስጦታ ወይም የኪራዩ ውል የተመዘገበበት ሰነድ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ይሆናል። ሆኖም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በገጠር መሬት ይዞታ ክርክር ተቃራኒ የጽሁፍ ማስረጃ የሚለውን የአዋጁን አገላለጽ በመደፍጠጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርን ለማስተባበል ማንኛውንም አይነት ማስረጃ መቀበል እንደሚገባ በሚከተለው መልኩ ወስኗል።[56]

*በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 24(4) እና ይህን አዋጅ ለማሰፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 20(4) የይዞታ ማረጋገጫ የያዘ ሰው የመሬቱ ባለይዞታ እንደሆነ ይደነግጋል። ይህ ማለት ግን በሕጉ የተቀመጠው የባለይዞታነት ግምት ሊስተባበል የማይችል በራሱ ብቻ አሳሪ ማስረጃ ስለመሆኑ የተመለከተ ነገር የለም።*

*በአንድ የፍትሐ ብሔር ክርክር በሕጉ በተለየ ሁኔታ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓቱ የተገደበ ካልሆነ በጽሑፍ፣ በምስክር፣ በህሌና ግምት፣ በተከራካሪዎች እምነት ወይም በማህላ ቃል ማስረዳት እንደሚቻል በፍ/ሕ/ቁ 2002፣ 1195፣ 1196 እና በተለያዩ ሕጎች ውስጥ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓቶችን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች አጠቃላይ አላማ፣ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል። በዚሁ መሰረት አመልካች ተጠሪዎች ይዞታየን ይዘውብናል እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎች የራሳቸውን መከራከሪያና በ1997 ዓ/ም የተሰጣቸውን የይዞታ ማረጋገጫ አቅርበዋል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያላቸውን ማስረጃ በመስማት እና ከሌላ የመንግስት አካላትም መቅረብ ያለበትን ማስረጃ በመቀበልና የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመዘን ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ሲገባው ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ያቀረቡ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም። የይዞታ ማረጋገጫም ቢሆን እንደ አንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለውና ሊመዘን የሚችል እንጅ ወሳኝ ማስረጃ (conclusive evidence) ሊይደለም...።*

በጸሐፊው እምነት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር፣ ስጦታ ወይም ከራይ የተመዘገበባቸው ሰነዶች የህዝብ ሰነዶች ናቸው። የህዝብን ሰነድን በቀላሉ ማስተባበል አይቻልም። ለዚህም ነው የአዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 24(4) ተቃራኒ የጽሁፍ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል የሚለው። የፍ/ሕ/ቁ 2010 የመንግስት (የህዝብ) ሰነዶችን ማስተባበል የሚቻለው ፍርድ ቤትን በማስፈቀድ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርን ለመቃወም የጠበበ ምክንያት ነው የሚኖረው። ይኸውም ተቃራኒ የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ ወይም በሙስና የተሰራ መሆኑን በመጠቆም/በቂ ማሳያ በማቅረብ ነው። በእርግጥ የይዞታ መረጋገጫ ደብተሩን ትክክለኛነት የሚያጠራጥሩ ሁኔታዎች ሲኖሩ ለትክክለኛ ፍትህ

[54] አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀጽ 17

[55] አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀጽ 18

[56] *ጥላሁን ንብዘ እና እነ መከተ ኃይሉ (2 ሰዎች)፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣(ቅጽ 13) መ/ቁ 69821፣ ታህሳስ 17/2004*፣ ለፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት እንደገና በማከራከር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት የተመለሰ።

ሲባል ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ጊዜ በሌላ መንገድ ለምሳሌ የሚመለከተውን ጽ/ቤት በመጠየቅ ተገቢውን ማጣራት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ግን እንደ ሰበር ችሎቱ አቋም ማንኛውንም ማስረጃ በማቅረብ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩን በመብት ደረጃ ማስተባበል ይቻላል ብሎ መደምደም ተገቢ አይመስልም።

በሌላ በኩል የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ባልተሰጠባቸው አካባቢዎች ክርክር የተነሳበት መሬት ባለይዞታ ማን ነው የሚለውም ነጥብ ለማጣራት ከሰነድ ማስረጃ ውጭ ያሉ የማስረጃ አይነቶችም ተቀባይነት ሊኖራቸው እንደሚችልም ልብ ማለት ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉ በገጠር መሬት ክርክር ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ አይነቶች እንደተያዘው ጭብጥ ይወሰናል። ለምሳሌ የመሬቱ መጠን/ስፋት አከራክሮ ከሆነ ባለሙያ ለክቶ እንዲያመጣ ሊታዘዝ ይችላል። ተከራካሪዎች መሬት በህገ ወጥ መንገድ የተሻሻጡ መሆን አለመሆኑ፣ የእኩል አራሽነት የተሰጠ መሆን አለመሆኑ፣ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሟች የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆኑ የሚሉ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ደግሞ የሰው ምስክር በመስማት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ አንዳንድ ጉዳዮች ደግሞ ከአንድ በላይ የማስረጃ አይነቶችን በመጠቀም የሚወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ተከሳሽ የከሳሽን መሬት ገፍቷል ወይስ አልገፋም የሚለው አከራካሪ ቢሆን መግፋት አለመግፋቱ በሰው ማስረጃ፣ ምን ያህል መሬት እንደገፋ መጠኑ ደግሞ በባለሙያ ተለክቶ እንዲቀርብ በማድረግ (በገላጭ ማስረጃ) ተረጋግጦ ሊወሰን ይችላል።

በአጠቃላይ እንደማንኛውም የፍትሐ ብሔር ክርክር በገጠር መሬት ክርክርም ተከራካሪዎች ክርክሮቻቸውን ያስረዱልናል የሚሏቸውን ማስረጃዎች መዘርዘር እና መጠቆም የእነሱ ድርሻ ነው።[57] በክርክር ወቅት የፍርድ ቤት ሚና የተወሰነ ነው። ይኸውም የሚያስፈልግ ከሆነ ሚዛኑን ጠብቆ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 249 እና 264 ተጨማሪ ምስክሮችን ጠርቶ መመርመር፣ በቁጥር 272 ቁሳዊ ማስረጃ መጠቀም ከፈለገ በራሱ ወይም በምትክ ዳኛ ማየት፣ በቁጥር 145 መሰረት ተከራካሪዎች የጠቆሟቸውን ሰነዶች ማስቀረብ፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 258 - 262 የማስረጃ አሰማም ሂደት ቅድሚያ ማስረዳት ያለበትን ወገን መለየት እና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን ነው።

ስለሆነም ማስረጃ መምረጥና የፈለጉትን ቀራቢነት ያለው ማስረጃ ለለተያዘው ጭብጥ የማቅረብ ሙቱት እና ግዴታ የተከራካሪዎች ነው። ይህ ማስረጃ የማቅረብ ሸክም (burden of production of evidence) ይባላል፡፡ ዋናው ግን በማስረጃ የማረጋገጥ ሸክም (burden of persuation) ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ተከራካሪ የፈለገውን ያክል ማስረጃ ቢያቀርብ የማሳመን ብቃት ከሌለው ዋጋ የለውም፡፡ በመሬት ክርክርም እንደማንኛውም ፍትሐ ብሔር ክርክር ሚዛን የደፋ (preponderance evidence) ያቀረበ ያሸንፋል። ስለሆነ ተከራካሪዎች ማስረጃ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ማሳመን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የማስረጃ ቀራቢነት እና የማስረጃው የማረጋገጥ አቅም (ክብደት) የተለያዩ መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል፡፡

በተግባር ግን ፍርድ ቤቶች ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ተቀባይነት እና ቀራቢነት ያለው ማስረጃ የትኛው ነው የሚለውን ሳይለዩ ቶሎ ብሎ የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤትን በማዘዝና በአግባቡ ሳያጣሩ ሲወስኑ ይታያሉ። ይህ ጽ/ቤት የሚሰጣቸው ማስረጃዎች አብዛኞቹ የሕግ መሰረት የሌላቸው፣ ህዝብ ተሰብስቦ የሚተቻቸው፣ የዳኝነት ስልጣንን የወሰዱና ተገቢነት የሌላቸው የማጣራት ዘዴዎች ናቸው የሚል ትችት ይሰጣል።[58]

[57] ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223

[58] ወርቁ ያዜ፣ ማስታወሻ ቁጥር 51፣ ገጽ 44 - 46፣ ስለዚህ ጽ/ቤቱ ወደ ፊት አቅሙ ሲጎለብት ሊሰጣቸው የሚችሉ በርካታ ማስረጃዎች ቢኖሩም ለጊዜው ግን ከአቅሙ በላይ ብዙ ነገሮች ስላሉ የተበላሹ እና አስተማማኝ ያልሆኑ ማስረጃዎች እየተላኩ ስለሆነ መጠንቀቅ ስፈልጋል በማለት ይደመድማል።

ሂደቱም ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ፣ የዜጎችን የመሰማት መብት ያጣበበ እና በተለይ አቅመ ደካሞችንና በህዝብ ተሰሚነት የሌላቸው ሰዎችን የጎዳ መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ።[59] ከዚህ አንፃር ጽ/ቤቱ ማስረጃ መላክ ያለበት ግራቀኙ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሰረት የጠየቁት ነገር ሲኖር ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 249 እና 264 መሰረት ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ ሲፈልግ፣ ወይም ከሙያ አንጻር የሚለካ፣ የሚታይ ነገር ሲኖር ሪፖርት እንዲልኩ ወይም ቀርበው እንዲያብራሩ ለማድረግ ነው። ስለሆነም  የጽ/ቤት ባለሙያ መታዘዝ ያለበት ባለሙያ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ብቻ ነው የሚለው ሀሳብ ሊሰመርበት ይገባል።

### 1.5 የገጠር መሬትን ሕጎች አለማክበር የሚያስከፈለው ቅጣት (እርምጃ)

የገጠር መሬት ሕግ ድንጋጌዎች አለማክበር በርካታ ቅጣቶች/እርምጃዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሚወሰደው እርምጃ ከግዴታዎች የሚመነጭ ነው፡፡ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች ግዴታዎችን አለመወጣታቸው አስተዳደራዊ፣ ፍትሐ ብሔራዊ እና የወንጀል እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው ያደርጋል፡፡ ግዴታዎችን ያልተወጣ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በመጀመሪያ ደረጃ እንደቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡[60] በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ስህተቱን ሊያርም ያልቻለ እንደሆነ ከተሰጠው የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በተጨማሪ ባለይዞታው በራሱ ድክመት መሬቱን ባለመንከባከቡ ምክንያት በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ የመጠቀም መብቱን መሬቱን ለመንከባከብ ግዴታ ለሚገባ ሌላ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በኪራይ እንዲሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በላይ የተቀመጠው አስተዳደራዊ እርምጃ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ በመሬት የመጠቀም መብቱን ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ካሳ ተከፍሎት መሬቱን እንዲለቅ እስከ መገደድ የሚደርስ እርምጃ ይወሰዳል፡፡[61] ግዴታዎችን ያልተወጣና አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶበት ራሱን ያላስተካከለ ሰው ከአስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በመሬቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡[62]

በሌላ በኩል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤትም ግዴታውን ካልተወጣ ፍትሐ ብሔራዊ ሀላፊነት ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለመስጠት ወይም ማንኛውንም አይነት ከመሬት ጋር የተያያዘ ምዝገባ ሲካሄድ በመዝጋቢው ስህተት ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ስህተቱ የሚመለከተው የመንግስት አካል የፍትሐ ብሔር ሀላፊነት ተጠያቂ ይሆናል፡፡ መስሪያ ቤቱም ካሳውን ከፍሎ ስህተቱን ከሰራው ባለሙያ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡[63]

ከዚህ በተጨማሪ የአዋጁ አንቀፅ 31 እና የደንቡ አንቀፅ 40 ማንኛውም ሰው አዋጁን ወይም ደንቡን ለማስፈፀም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ ያለበት መሆኑንና አዋጁን ወይም ደንቡን የጣሰ ወይም አፈፃፀመን ያስናከለ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆን ይደነግጋሉ፡፡ አግባብ ያለው ወንጀል ሕግ የሚባለው ደግሞ ለምሳሌ የደን፣ የአካባቢ ጥበቃ እና የዱር አራዊት ጥበቃ አዋጆች ከገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ የወንጀል ድንጋጌዎች አሏቸው፡፡ የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግም በሌላ ሰው የይዞታ መሬት የሚገኘውን ሳር፣ ግጦሽ፣

[59] ደሴ ስዩም፣ ማስታወሻ ቁጥር 42፣ ገጽ 50 - 53
[60] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 21(1)
[61] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 21(2)
[62] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 21(5)
[63] አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀፅ 23(7)(8)፤ ይህም ከፍ/ሕ/ቁ 1198 ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

የእርሻ ስፍራ፣ ደን፣ የአትክልት ቦታም ሆነ በማናቸውም ሌላ አይነት ሁኔታ የሚገኝ መሬት ላይ መንጋዎችን አሰማርቶ ያስጋጠ፤ የሌላ ሰውን መሬት የወረረ ወይም ሁከት ያደረሰ፤ የግል ወይም የህዝብ የሆነውን የዉኃ አወራረድ የለወጠ፤ የሌላ ሰውን መሬት ወሰን ያፈረሰ፤ ሰብልን፣ ግጦሽንና አካባቢን የበከለና የመሳሰሉትን ጥፋቶች የፈጸመ እንደሆነ በወንጀል ተከሶ ሊቀጣ የሚችል መሆኑን ይደነግጋል።[64]

## 2. የገጠር መሬት ክርክርን በተመለከተ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ከሚቀርቡ ጉዳዮች ውስጥ እጅግ የሚበዛው የመሬት ክርክር ነው፡፡ ክርክሮቹ ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የሚዘልቁና መቋጫ የሌላቸው ሲሆኑ ይስተዋላሉ። ፍርድ ቤቶች በዚህ የበዛ የመዝገብ ክምችት ውስጥ ደፋ ቀና ይላሉ። ግን ደግሞ ፍትህ በትክክለኛ እና በሚፈለገው መንገድ እየተሰጠ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ይፈጥራል፡፡ በርካታ የተዛቡ ውሳኔዎች እንደሚሰጡ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡[65] በርካታ ትክክለኛ ውሳኔዎች ደግሞ ከብዙ ድካም በኋላ የተገኙ ናቸው፡፡ መቋጫ የለሽ ለሆነ የመሬት ክርክር ወይም የተዛባ ፍርድ መንስኤዎች ምንድን ናቸው የሚለው ራሱን በቻለ ጥናት መመለስ ያለበት ቢሆንም ከፍርድ ቤቶች አንጻር ግን በእያንዳንዱ የክርክር ሂደት ሕጉን በአግባቡ አለመረዳት፣ መያዝ ያለበትን ጭብጥ ካለመለየት፣ ተለይቶ የተያዘን ጭበጥ ከቀረበው ማስረጃ ጋር አለማያያዝ፣ ጭብጡን፣ ማስረጃውንና ሕጉን በአግባቡ አለማገናኘት፣ የማስረጃን ታማኝነት በትክክል ካለመመርመርና በአጠቃላይ በማስረጃ ምዘና ላይ ከሚታዩ እጥረቶች የተነሳ መሆኑን መጠቆም ይቻላል። ስለሆነም በገጠር መሬት ይዞታ ክርክር ውስጥ አከራካሪ ጭብጥን ከመያዝ ጀምሮ ጉዳዩ በውሳኔ እስከሚቋጭበት ጊዜ ባለው ሂደት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች በመነሳት መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡

### 2.1 ክርክርን በአግባቡ ያለመምራት፣ ተገቢውን ጭብጥ ያለመያዝና በተገቢው ማስረጃ አጣሪቶ ያለመወሰን ችግር

እንደማንኛውም ክርክር የገጠር መሬት ክርክርም በዋነኛነት በፍሬ ነገሮች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከሳሾች እና ተከሾች በሕግ ጉዳይ ከሚለያዩት ይልቅ በአብዛኛው በፍሬ ነገሮች ላይ ይለያያሉ። ፍሬ ነገሮች (facts) ሰዎች በስሜት ህዋሳቶቻቸው የሚለዩአቸው ወይም የሚገነዘቧቸው ነገሮች ወይም ኩነቶች ናቸው፡፡

በገጠር መሬት የይዞታ ክርክር ሂደት አጨቃጫቂ የሆኑ ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን በመለየት አግባብነትና ቀራቢነት ባላቸው የማስረጃ አይነቶች ለማረጋገጥ እንዲቻል ዳኞች በቅድሚያ ለቀረቡት ክርክሮች የማዕዘን ድንጋይ የሆኑትን ፍሬ ነገሮች መለየት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ የይዞታ ክርክር ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ደግሞ አግባብነት ካላቸው መሰረታዊ የመሬት ሕጎች፣ ከተከራካሪዎች የጽሁፍ አቤቱታዎች፣ ተከራካሪዎች በቃል ክርክር ከሚያነሱት እና በማስረጃነት ከሚያቀርቧቸው ሰነዶች የሚፈልቁ ናቸው፡፡

ዳኞች ጭብጥን ከመያዛቸው ማስረጃ ከማዘዛቸው በፊት በቅድሚያ በቀረበው ክስ ላይ ከሳሽ ለአቤቱታው መሰረት አድርጎ የሚጠቅሳቸውን ፍሬ ነገሮች መመርመርና መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ በከሳሽ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮችን የመሬት ሕጎች ከሚደነግጉት መብት ጋር በማገናዘብ በትክክል የክስ ምክንያት (cause of action) ስለመኖሩ መለየት ተገቢ ነው፡፡ የገጠር

[64] የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 414/1996፣ አንቀጽ 685 - 688 እና 516 - 519

[65] ዓሊ መሀመድና ማሩ ባዘዘው፣ *የመሬት ባለይዞታና ተጠቃሚ የመሆን መብት በኢትዮጵያ፣ ነሐሴ 2002 (ያልታተመ)*፣ ገጽ 94 - 96

መሬት ሕጎች ከሚሰጡት መብት አንጻር ከሳሽ ምን እንተደረገ፣ ምን ሳይደረግ እደቀረ እና ምን ሊደረግለት እንደሚገባ በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል። በሌላ አገላለጽ በገጠር መሬት ክርክር ሂደት የሚቀርቡ የጽሁፍና የቃል አቤቱታዎችን ይዘት መረዳት ያስፈልጋል። እንደሌላው የፍርድ ቤት ክርክር ከሳሽና ተከሳሽ አቤቱታቸውን የሚያቀርቡት በጽሑፍ ነው።[66] ከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮችና ነገሮቹ የተፈጠሩበትን ጊዜና ስፍራ፣ ክስ እንዲያቀርብ ያደረገውን ምክንያት፣ ደረሰብኝ የሚለውን በደል ወይም የመብት ጥሰት፣ ካቀረበው የክስ ምክንያት ጋር ተከሳሽ እንዴት እንደሚገናኝ፣ ፍርድ ቤቱ እንዲሰጠው የሚፈልገውን ዳኝነት መግለጽ እና እነዚህን ፍሬ ነገሮች ለማረጋገጥ አሉ የሚላቸውን ማስረጃዎች እና የትኛው ማስረጃ ለየትኛው ፍሬ ነገር እንደሚያስረዳ በመግለጽ አባሪ ማድረግ አለበት።[67]

እነዚህን ነገሮች አሟልቶ የቀረበን ክስ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ወይም ዳኛው መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች (technical and legal sufficiency) ካረጋገጡ በኋላ[68] ተከሳሽ መልሱን በጽሑፍ እንዲያቀርብ ይደረጋል። ተከሳሽም መቃወሚዎች ካሉት በቅድሚያ በመግለጽ፣ በፍሬ ነገሩ ላይ በግልጽ በማመን ወይም በመካድ ወይም በከፊል በማመን ወይም በመካድ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ካለው በግልጽ በማስቀመጥ፣ ማስተባበያ ማስረጃዎች ካሉት አባሪ በማድረግ ማቅረብ ይኖርበታል።[69] መልሱም በተገቢው መንገድ መሟላት ያለበት ሁሉ አሟልቶ ካልቀረበ ዳኛው አይቶ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።[70]

ክስ በሚሰማበት ወቅት የግራቀኙን መቅረብ ማረጋገጥ፣ ክስና መልስን ማንበብና በሚገባ በቅድሚያ መረዳት፣ ከሳሽ የሰነዘራቸው ፍሬ ነገሮች ከመሰረታዊ የመሬት ሕጎች አንጻር በመያዝ ተከሳሽ በግልጽ ያላመነውን ወይም ያልካደውን ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ መጠየቅ እና የታመነና የተካደውን መለየት ያስፈልጋል።[71] ይህ ሂደት ክርክሩን ለመቋጨት የሚያዝ ጭብጥና የሚቀርብ ማስረጃ ለመለየት በጣም አስፈላጊ ነው።

ጭብጥ ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በፍሬ ነገር ወይም በሕግ ጉዳዮች ላይ በመለያየታቸው ምክንያት ፍርድ ቤቱ የሚጸና ፍርድ ለመስጠት እንዲቻለው በማስረጃ እንዲያረጋግጥ ለይቶ የሚይዘው ነጥብ ነው።[72] ጭብጦች የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም ጭብጦች አንዳንድ ጊዜ ዋናውን የክርክር ጉዳይ የማይመለከቱ እንደ ቅድመ ሁኔታ ወይም በተጓዳኝነት የተነሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ጉዳዩ በፍርድ አልቋል፣ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም እና በይርጋ ታግዷል የሚሉ ክርክሮች ቢነሱ ቅድሚያ የሚፈቱ ተጓዳኝ ጭብጦች ናቸው። ስለሆነም ወደ ሙሉ የፍሬ ጉዳይ ወይም የሕግ ጉዳይ ክርክሮች ከመሄዳችንና ዋናው ሙግት (trial) ተጀምሮ ማስረጃ ከማዘዛችን በፊት በትክክል መያዝ ያለበት ተጓዳኝ ጭብጥ ተመስርቶ እልባት መሰጠት ይኖርበታል። ለምሳሌ ሸለማ መንግስቱ እና ፋይሳ መንግስቱ በተከራከሩበት ጉዳይ[73] ከሳሽ በወረዳ ፍ/ቤት የይዞታ መሬቴን ይልቀቅልኝ የሚል ክስ ሲያቀርብበት ተከሳሽ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል መቃወሚያ አቅርቧል። ሆኖም የወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ ቀጣዮቹ ፍርድ ቤቶች ይርጋውን በዝምታ በማለፋቸው ከአድካሚ ክርክር በኋላ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ወስኗል። የወረዳ ፍርድ ቤቱ በወቅቱ መያዝ ያለበትን ተጓዳኝ ጭብጥ ይዞ ቢያከራክር ኖሮ ጉዳዩ በአጭር ሊቋጭ የሚችልበት አጋጣሚ ነበር ማለት ነው።

---

[66] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 80 - 93 እና 222 - 240

[67] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222(ነ)(ረ)(ሸ)፣ 240 እና 225

[68] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 229 እና 231

[69] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234፣ 244፣ 235 እና 223

[70] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 238፣ 229 እና 234

[71] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 241

[72] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 247

[73] *የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 69302፣ ታህሳስ 20/2004 ዓ/ም*

ዋናው ጭብጥ ደግሞ ዋና ዋና የክስ ምክንያቶችን (cause of actions) የተመለከተ ይዘት ያላቸው ነጥቦች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። ይህን ለመለየት ዳኞች የመሬትን ሕጎች በሚገባ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ተከራካሪዎች ከሕጉ አንጻር ፍሬ ነገሮችን በሚገባ ማቅረብ አለባቸው። ጭብጥ የሚመሰረተው ከክሱ እና ከመልሱ በመነሳት፣ በተከራካሪዎች የሰነድ ማስረጃዎች እና በክስ መስማት ቀን ፍርድ ቤቱ ከሚያደርገው ምርመራ ነው።[74] ዳኞች ክስን በአግባቡ ሰምተው መያዝ ያለባቸውን ተዓዳኝና ዋና ጭብጦች መለየት ከቻሉ የክርክሩ ግማሽ መንገድ ተጠናቀቀ ማለት ነው።

ከዚህ ላይ አንድ ምሳሌ እንመልከት፤ ከሳሽ ወ/ሮ አገኘሁ ሆነ እና ተከሳሾች ፣ኛ አቶ አይሸሹም አቸነፍ፣ 2ኛ ወ/ሮ በለጡ አስፋው ከአብናት ወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በተከራከሩበት ጉዳይ[75] የስር ከሳሽ የመሬት አዋሳኝና ጎጥ በመጥቀስ ከ፣ኛ ተከሳሽ ጋር በ1989 ዓ/ም የተደለደልነውና በ1990 ዓ/ም ስንፋታ የደርሰኝን 2 ጥማድ መሬት ለ፣ኛ ተከሳሽ በአበል አከራይቸው የነበረ ቢሆንም ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ሲጋባ መሬቱን እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፍቃደኛ ስላልሆነ እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት አቅርባለች፡፡ የስር ፣ኛ ተከሳሽ እኔ የያዝኩት የራሴን ድርሻ ነው፤ የከሳሽን ድርሻ የያዘች 2ኛ ተከሳሽ ናት፤ ልጠየቅ አይገባም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በበኩሏ ክስ ከቀረበበት መሬት ከ፣ኛ ተከሳሽ ጋር ተጋበተን ስንር መስማማት ስላልቻልን ስንፋታ ግማሽ ጥማድ ደርሶኝ በይዞታ ደብተር አስመዝግቤ የያዝኩት ስለሆነ ልጠየቅ አይገባም በማለት አቅርባለች፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤቱ ክርክር የተነሳበት መሬት የማን ነው? የሚለውን ጭብጥ ይዞ የወረዳውን መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ማስረጃ ከጠየቀ በኋላ ምንም እንኳን 2ኛ ተከሳሽ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሬቱን ከ፣ኛ ተከሳሽ ጋር ተካፍላ የያዘች ቢሆንም አስቀድሞ ፣ኛ ተከሳሽና ከሳሽ የነበራቸው ጋብቻ ሲፈርስ ለከሳሽ የደረሳት መሆኑ ስለተረጋገጠ 2ኛ ተከሳሽ ክስ የቀረበበትን መሬት ለከሳሽ ልታስረክብ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብትጠይቅም ቅሬታዋ ተሰርዟል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ስታቀርብ ችሎቱ ክርክር የተነሳበት መሬት የአመልካች ነው ወይስ የተጠሪ? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ ይህ መሬት ፣ኛ ተከሳሽ እና ተጠሪ (የሥር ከሳሽ) የነበራቸው ጋብቻ ሲፈርስ ለተጠሪ የደረሳት ቢሆንም አመልካች በፍርድ ያገኙቸው ሆኖ እያለ የተጠሪ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ሽሮታል፡፡

የግራቀኙ ክርክር በአጭሩ ሲታይ ከሳሽ እንዲለቀቅላት የጠየቀችው የመሬት መጠን 2 ጥማድ ነው። ፣ኛ ተከሳሽ ይህን አምኖ እሱ አለመያዙን ገልጿል። በአበል ስለመያዝ አለመያዙ ግን ያለው ነገር የለም። 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ይህ መሬት የተከሳሾች የጋራ ሆኖ ስንፋታ ግማሽ ጥማድ ደርሶኛል በማለት ተከራክራለች። ከዚህ የምንረዳው በሁለቱም ፍርድ ቤቶች ስለ 1.5 ጥማድ መሬት ምንም ሳይሉ መቅረታቸውን፣ በጭብጥነትም ያልተያዘ መሆኑን፣ ፣ኛ ተከሳሽ በአበል የያዘ መሆን አለመሆኑ፣ ተከሳሾች የተካፈሉት መሆን አለመሆኑን፣ ተካፍለውት ከሆነ የከሳሽን መብት የሚያስቀር መሆን አለመሆኑ ያልተጣራ መሆኑና በአጠቃላይ ተገቢውን ጭብጥ ይዘው አጣርተው አለመወሰናቸውን ነው፡፡

በተገቢው መንገድ ጭብጥ ይዞ አለመከራከር ደግሞ ጉዳዮች በበላይ ፍርድ ቤቶች ሲታዩ እንደገና አከራክረው እንዲወስኑ ስለሚመለሱ የፍርድ ቤትና የተከራካሪዎች ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ የሚያባክንና አሰልች ለሆነ ክርክር የሚደረግ ይሆናል፡፡

[74] የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 248

[75] *የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 03-16263*

በዚህ ረገድ ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምረው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚያም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሰው ወደ ወረዳ ፍርድ ቤቶች እንደገና አከራክረው እንዲወስኑ የሚመልሷቸው በርካታ የገጠር መሬት ክርክሮች እንዳሉ ሆኖ ከዚህም አልፎ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይቀር ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት እንደገና ክርክር እንዲደረግ የሚመለሱ መዝገቦች ቁጥር ቀላል አይደለም።[76] በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ከሚወስኑት የገጠር መሬት ክርክሮች ውስጥ ቢያንስ ግማሽ የሚሆኑት መዝገቦች ወደ ሥር ፍርድ ቤቶች እንደገና እንዲያከራክሩ ጭብጥ ተይዞ የሚመለሱ ናቸው።[77]

ሌላው ከማጣራት ጋር የተያያዘው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የሚሰጣቸው ማስረጃዎች ወጥ ያለመሆንና ብሎም በአንድ ጉዳይ ሁለትና ከዚያም በላይ የተለያዩ ማስረጃዎች የመስጠት ችግር ነው። ፍርድ ቤቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የጽ/ቤቱን ማስረጃ አሰጣጥ እገዛዎች መፈለጋቸው የማይቀር ቢሆንም በተመረጡ ጉዳዮች ብቻ መታዘዝ አለበት። ጽ/ቤቱ በታዘዘ ጊዜ የሚላከው ማስረጃ ግልፅ ካልሆነና አከራካሪ ሁኔታ ካጋጠመ ፍርድ ቤቶች ተጨማሪ ማብራሪያ በመጠየቅ በአግባቡ ማጣራት አለባቸው።

### 2.2 ከቤተሰብ አባልነት እና ጧሪ ተንከባካቢ አወራረስ ጋር የተያያዙ ችግሮች

የቤተሰብ አባል ማለት ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖርና የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው የይዞታ ባለመብቱን አርሶ አደር ገቢ በመጋራት የሚተዳደር ማንኛውም ሰው ነው።[78] የቤተሰብ አባልነት ክርክር ሲነሳ ፍርድ ቤቶች ብዙ ጊዜ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት አጣርቶ ማስረጃ እንዲልክ ሲያዙ ይታያል። ሆኖም በሕጉ በተቀመጠው ትርጉም መሰረት ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሆነ ሰው የሟች የቤተሰብ አባል ነው ወይስ አይደለም የሚለው የሚያረጋግጠው በፍርድ ቤት የግራቀኝ ምስክሮችን በመስማት መሆን ይኖርበታል። በሌላ በኩል አንዳአንድ ፍርድ ቤቶች የቤተሰብ አባል የሚባለው መሬት በተደለደለበት ወቅት አብሮ መሬት የተደለደለን ሰው ነው የሚል ድምዳሜ ሲደርሱ ይታያል። ሆኖም በሕጉ በተቀመጠው መልኩ የቤተሰብ አባል የግድ መሬት ሲደለደል አብሮ የነበረ መሆን አይጠበቅበትም። እንዲያውም መሬት ሲደለደል (1983 ወይም በ1989 ዓ/ም እንደአካባቢው ሁኔታ) አብሮ ቤተሰብ የነበረ ሰው ከጊዜ በኋላ የራሱ ገቢ ያለው ሰው ሆኖ ትርጉሙን ላያሟላ ይችላል። በአንፃሩ በድልድሉ ወቅት ያልነበረ ወይም ያልተወለደ ሰው ከጊዜ በኋላ የቤተሰብ አባል ሊሆን ይችላል። ከዚህ አንፃር ፍርድ ቤቶች ከሰሽ ወይም ተከሳሽ የቤተሰብ አባል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ምስክሮችን ሰምተው ሲመዝኑ መነሻ ነጥባቸው ሟች የሆነው ሰው በሞተበት ወቅት የሕጉ ትርጉም ተሟልቷል ወይስ አልተሟላም የሚለው መሆን ይኖርበታል።

ለምሳሌ በጃቢጣህንና ወረዳ  ፍርድ ቤት አንችነሽ በላይ እና ቄስ ብርሀኔ ምህረት በተከራከሩበት ጉዳይ[79] ከሳሽ ከአያቴ እማሆይ ወንዴ ጥሩነህ ጋር በ1989 ዓ/ም በቤተሰብ አባልነት ተደልድየ አብሬ ያደግሁ ቢሆንም አሁን ግን አያቴ ስትሞት

---

[76] ለምሳሌ *ካሳሁን ሀብቱና እናትፈንታ ቢረሳው፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 85128፣ የካቲት 29/2005 ዓ/ም*፤ የስር ፍርድ ቤቶች ተገቢውን ጭብጥ ይዘው አጣርተው አልወሰኑም ተብሎ ለአየሁ ጓጉሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ተመልሷል። *ቄስ ሰሜ በላይ እንየው እና ፋሲካው ሸምላ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 85863፣ ሚያዚያ 09/2005 ዓ/ም*፤ ለቄሪት ወረዳ ፍርድ ቤት የተመለሰ፣ በተመሳሳይ *ሁኔታ ጥላሁን ጐጉሳ እና መከተ ሃይሉ (2 ሰዎች)፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 69821፣ ታህሳስ 17/2004 ዓ/ም*፣ ለፎገራ ወረዳ ፍርደ ቤት የተመለሰ።

[77] ጸሐፊው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲሰራ የተገነዘበው

[78] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 2(6)

[79] *የጃቢጣህናን ወረዳ ፍርድ ቤት መ/ቁ 13693፣ ሰኔ 21/05 ዓ.ም* የተወሰነ እና *በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ 15-8588 ሐምሌ 18/2005 ዓ/ም* በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ ቅሬታው የተሰረዘ።

ተከሳሽ መሬቶቹን የያዘብኝ ስለሆነ ይልቀቅልኝ በማለት ክስ አቅርባለች። ተከሳሽ በበኩሉ ከሳሽ በ1989 ዓ/ም ባል አግብታ ስለሄደች አልነበረችም፤ በወቅቱ ከሟች እናቴ ጋር መሬት የተደለደልኩት እኔ ነኝ በማለት ተካራክሯል። የወረዳ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ በመያዝ በግራቀኙ ምስክሮች ያጣራው ሟች በሞተችበት ወቅት ከሳሽ የቤተሰብ አባል ነበረች ወይስ አልነበረችም የሚለውን ሳይሆን ከሳሽ ከሟች ጋር በ1989 ዓ/ም ቤተሰብ ሆና አብራ መሬት ተደልድላለች ወይስ አልተደለደለችም የሚለውን ነው። ሆኖም ከላይ በተገለጸው አግባብ ዋናው የክርክሩ አንኳር መሆን ያለበት በ1989 ዓ/ም አብሮ መደልደል አለመደልደል ሳይሆን ሟች በሞቱበት ወቅት የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆን ነው።

ሌላው አብሮ ነዋሪ ወይም ጧሪ ተንከባካቢ ያለ ኑዛዜ መውረስ ይቻላል ወይ? የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል። ሕጉ ትርጉም የሚሰጠው ለአብሮ ኑዋሪ ተንከባካቢ ሳይሆን ለተጧሪ ነው። "ተጧሪ" ማለት በዕድሜ መግፋት፣ በበሽታ፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ሳቢያ በራሱ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት የተሳነውና ለመተዳደሪያው የሌሎች ሰዎችን ዕርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ነው።[80]

*በአየሁ ጓጉሳ ወረዳ ፍርድ ቤት እናትፈንታ ቢረሳውና ካሳሁን ሀብቴ* በተከራከሩበት መዝገብ[81] ከሳሽ የሟች አጎቴ አድማስ ወንድምን መሬት ወራሽነቴን አረጋግጬ ለሌላ ሰው አከራይቸ የያዝኩትን መሬት ተከሳሽ ወራሽ ነኝ በማለት ወራሽነት አሳውጆ የያዘብኝ ስለሆነ እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርባለች። ተከሳሽ በበኩሉ ከሳሽ ሟችን ጧሪ አለነበረችም፤ ተከሳሽ ከእኔ የተሻለ ዝምድና የላትም፤ እኔ ጧሪ በመሆኔ ፍርድ ቤቱ አውርሶኛል በማለት ተከራክሯል። የወረዳ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ምስክሮች በመስማትና የግራ ቀኙን የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማየት ከሳሽ በደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀፅ 11(7)(መ) ጧሪ ተንከባካቢ በሚለው ወራሽነት አውጥታለች። ተከሳሽ ግን በአንቀጽ 11(7)(ሐ) ወራሽነት አውጥቷል። የዝምድና ደረጃቸው ሟች ለሁለቱም አጎት ነው። የከሳሽ ምስክሮች በተሸለ ሁኔታ ከሳሽ የሟች ጧሪና ተንከባካቢ የነበረች መሆኑን ያስረዱ ስለሆነ እና ከሳሽ በትክክለኛው ድንጋጌ ወራሽነት ስላሳወጀች መሬቱ ለከሳስ ይገባል በማለት ወስኗል።

ሆኖም ከአዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀፅ 16(5)(6) እንደምንገዘበው ሟች ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ መሬቱ በውርስ የሚተላለፈው በደንቡ በሚወሰን ቅደም ተከተል መሰረት ለልጆች፣ ለቤተሰብ አባላት እና ለወላጆች ነው።[82] የደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11(7) ቅደም ተከተል ስናይ አዋጁ ላይ ሊወርስ የማይችል አብሮ ነዋሪ ተንከባካቢ የሚል ሐረግ በፊደል "መ" ስር ገብቷል። ይህ የአዋጁን መንፈስ ያልተከተለና ተገቢነት የሌላው አገላለፅ ነው። ስለሆነም ጧሪ ተንከባካቢ ሊወርስ የሚገባው በኑዛዜ ወይም በስጦታ ብቻ ነው። ለምሳሌ የአዋጅ አንቀፅ 17(1)(ለ) ስጦታ ለመቀበል አንዱ መስፈርት መጦር ነው። በተጨማሪም ከአንቀፅ 16(1)-(3) ሕጉ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ለሚያሟላ ማንኛውም ሰው በኑዛዜ ማስተላለፍ ይቻላል። ከዚህ ስንነሳ የሕጉ አላማ አንድ ሰው ለሚጦረው ሰው በህይወት እያለ በስጦታ ካልሆነም ከመሞቱ በፊት በኑዛዜ

---

[80] አዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 2(4)

[81] *የመ/ቁ 2216/05፣ ሚያዝያ 01/2005 የተወሰነ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 85128 የካቲት 29/2005 ዓ/ም* ከመለሰው በኋላ

[82] አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀፅ 16(5) አንድ የመሬት ባለይዞታ ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ መብቱ በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ መተዳደር ለሚፈልግ የሟች ልጅ ወይም ቤተሰብ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት ይተላለፋል በማለት ይደነግጋል። የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 16(6) ልጅ ወይም ቤተሰብ የሌለው እንደሆነ ወላጆቹ በክልሉ ውስጥ ነዋሪዎች ሆነው በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የሚፈልጉ ከሆኑና አስቀድሞ ያላቸው የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ከከፍተኛው የይዞታ መጠን በታች መሆኑ ከታወቀ የመሬት ይዞታውን የመውረስ መብት ይኖራቸዋል በማለት ይገልጻል።

መሬቱን በማስተላለፍ ሊጠቅመው ይችላል የሚል ነው፡፡ ከዚህ ወጭ ሳይናዘዝ ከሞተ ሕጉ ማስተላለፍ የሚፈልገው ለልጆች፣ ለቤተሰብ አባላትና ለወላጆች (በደንብ በሚወሰን ቅደም ተከተል) ነው፡፡ ደንቡ ደግሞ አዋጁን የሚያቃርን ዝርዝር መያዝ አይኖርበትም፡፡

### 2·3 አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን በፍርድ ቤት ከሚወሰኑ ጉዳዮች ያለመለየት ችግር

አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች እና በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች አስተዳደራዊ እና ፍትሐብሔር ነክ ክርክሮችን ለይቶ ያለማወቅ ችግር ያጋጥማል፡፡ ለምሳሌ በክልላችን ከቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ውሳኔ በመነሳት ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በደረሱት የመዝገብ ቁጥር 42747 እና 43722 መረዳት እንደሚቻለው ግለሰቦች የመሬቱ ባለይዞታ እኔ ነኝ እኔ ነኝ በማለት በሚከራከሩበት ጉዳይ የቀበሌው ኮሚቴዎች ለአንደኛው ተከራካሪ ወገን ይገባል በማለት ውሳኔ በመስጠታቸው በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘው ወገን ለወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የፀናበት በመሆኑ ይግባኙን ለወረዳ ፍርድ ቤት ሲያቀርብ የወረዳ ፍርድ ቤቱም የጽ/ቤቱን ውሳኔ እንዳለ አጽንቶታል። ሆኖም ይግባኙ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ያቀረቡት ክርክር የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ስለሆነ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ከሚባሉት ውስጥ የሚመደብ አይደለም፡፡ የቀበሌው ኮሚቴዎችም ሆነ የወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በግራቀኙ የመሬት ባለይዞታነት ክርክር ላይ የሰጡት ውሳኔ ከስልጣናቸው ውጭ ስለሆነ የሚፀና አይሆንም፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤቱም ቢሆን ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ ተቀብሎ ማከራከር አልነበረበትም በማለት ውሳኔውን በመሻር በመሬቱ ላይ ሙበት አለኝ የሚል አካል ስልጣን ላለው የወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ የሚችል መሆኑን በመግለጽ ወስኗል፡፡

አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በሕጉ በግልፅ ባይቀመጥም ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የወረዳ ጽ/ቤትና ከቀበሌ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር በመነሳት ምን አይነት ጉዳዮችን እንደሚያካትት መረዳት ይቻላል፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 20 እና በደንቡ አንቀፅ 16 ሥር የመሬት ተጠቃሚዎች እና ባለይዞታዎች ግዴታዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህም በይዞታም ሆነ በኪራይ የያዘውን መሬት የመንከባከብ፣ መሬቱ አከባቢ ዛፍ መትከልና ተንከባክቦ ማሳደግ፣ በአስተራረስ ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መያዝና የመሳሰሉትን ያካትታል። እነዚህን ግዴታዎች የማያከብር የመሬት ባለይዞታ ምን አይነት እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል በአዋጅ አንቀጽ 21 እና በደንቡ አንቀጽ 17 ስር ተዘርዝረዋል፡፡ በመጀመሪያ የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በቅደም ተከተል ይሠጠዋል፡፡ ስህተቱን ካላረመ መሬቱን ያልተንከባከበ ከሆነ መንከባከብ ለሚችል ሰዉ በኪራይ ለተወሰነ ጊዜ ጊዜ ይሰጣል፡፡ በዚህ የማይስተካከል ከሆነ መሬቱን ይነጠቃል፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ በመሬቱ ላይ ላደረሰዉ ጉዳት በፍትሐ ብሔር ሕግ ሊወሰንበት ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ[83] የጠውን ትርጉም መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

> *…በመሰረቱ በአዋጅ አንቀጽ 21 ሰር የተዘረዘሩት እርምጃዎች ሁሉም አስተዳደራዊ ናቸዉ የሚል እምነት የለንም። ምክንያቱም ለምሳሌ በአዋጅ አንቀጽ 21 (5) መሰረት የመሬት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ላደረሰዉ ጉዳት በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ካሳ እንድከፍል ሊወሰንበት የሚችል ቢሆንም ካሳዉ የሚወሰነዉ በአስተዳደራዊ ዉሳኔ ሳይሆን በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶበት ነዉ፡፡ …አንዳንድ ጊዜ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚወሰድባቸዉና በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ የሚችሉ ጉዳዮች ሲቀላቀሉ ይታያሉ፡፡*

[83] *ሰከላ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አመቃቀም ጽ/ቤት እና ዘመኑ ያረዴ፣ መ/ቁ 48849፣ መጋቢት 10/2004 ዓ/ም*

*አስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚወሰድባቸዉ ጉዳዮች በአዋጅ በአንቀጽ 20 እና በደንቡ አንቀፅ 16 ሰር የተዘረዘሩት መሬትንና የአከባቢ ብዝሃ ህይዎት ከመንከባከብና ከአስተራረስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ብዙም ክርክር አያስነሱም። ይልቁንስ ብዙ ጊዜ ክርክር የሚነሳባቸዉ በአዋጁ አንቀፅ 20(1)(ረ) እና በደንቡ አንቀፅ 16(1)(ሠ)(ረ)(ሰ) የተዘረዘሩት ወሰናቸዉ ተለይቶ የተከለለ መሬቶችን ድንበር የገፋ ወይም ተለይተዉ የታወቁ መንገዶችን የዘጋ ወይም የወል መሬቶችን ወሰን የገፋ ሰው ቢኖር ስለሚወሰደዉ እርምጃ ነዉ። በእኛ እምነት እነዚህን ጥፋቶች የሰራ ባለይዞታ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላል። ነገር ግን የሚወሰደዉ እርምጃ ክርክር የሚያስነሳ ጉዳይ ላይ መሆን የለበትም። ማለትም አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድብት ሰው ወሰን አፍርሰሃል፣ የወል መሬት ገፍተሃል ወይም መንገድ ዘግተሃል የተባልኩት በሀሰት ነዉ። የእኔ የይዞታ መሬት ነዉ እያለ የሚከራከር ቢሆን ጉዳዩ መፈታት ያለበት ሕጉን ተከትሎ በሚደረግ ክርክርና ማስረጃ መሰረት በፍርድ ቤት መሆን ይኖርበታል። በሌላ አገላለጽ ይህ ግለሰብ ማስረጃ አቅርቦ መንገድ የተባለዉ፣ ወይም ገፋህ ተባለዉ የወል መሬት የእርሱ መሆኑን ሊያሳይ የሚችል ነዉ። ነገር ግን ተለይቶ ታወቀና ክርክር የማያስነሳ ከሆነ በሕጉ የተቀመተዉን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት መሬቱን ሊለቅ ይችላል፤ በማለት ወስኗል።*

### 2.4 ሕገ ወጥ ዉሎችን እውቅና ከመስጠት ጋር የተያያዙ ችግሮች

የፀደቀና ሕጋዊ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ጥናትና ማስተር ፕላን ባለመኖሩ ምክንያት በእርሻ መሬቶች ላይ የተለያዩ ግንባታዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ። የገጠር መሬት አዋጁንና ሕገ መንግስቱን በተላለፈ ሁኔታ በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ደግሞ በሚፈጠሩ ጥንስስ ከተሞች አንዳንድ ባለይዞታዎች የይዞታ መሬታቸውን ከሕግ ውጭ ከተማ ለሚቆረቁሩ ግለሰቦች በመሸጣቸው ለግጭት ከመዳረጉ ባሻገር ለመልካም አስተዳደር መጓደል ምክንያት እየሆነ መጥቷል። ለምሳሌ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገ የዳሰሳ ጥናት መሰረት በተለያዩ ሽፋኖች የመሬት ሽያጭና ዝውውር የተበራከተ መሆኑን በሚከተለው መልኩ ይገለጻል።

> *...ተከራካሪዎች የሐሰት የብድር ውል ይዋዋላሉ፣ በውሉ መሠረት ገንዘቡ ስላልተከፈለኝ በመያዣነት የያዝኩት መሬት ሰመ ንብረትነቱ ይዛወርልኝ ተብሎ ዳኝነት ይጠየቃል። ፍርድ ቤቶችም በዚሁ መሠረት ባዶ መሬት ይተላለፍ እያሉ ይወስናሉ። ይህ በሕገ-መንግስቱ ስለመሬት በግልጽ የተደነገገውን መርህ መጣስ ነው። የችግሩን ግዝፈት ለማየት ሁለት አብነቶችን እናያለን።*
>
> 1. *ላሊበላ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ እማሆይ አስላኩ ኃይሌ የተባሉ በ4 የተለያዩ መዝገቦች ገንዘብ ተበድረው አልከፈሉም ተብሎ ክስ ቀርቦባቸው አምነው ከነበራቸው የከተማ ቦታ 150፣ 150፣ 200 እና 300 ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ አበዳሪ ለተባሉት (እውነታው ግን የመሬት ሽያጭ) ለብድሩ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ተወስኖ ሰመ ንብረት እንዲዘወር ካርታና ፕላን ተሰርቶ እንዲሰጣቸው ጭምር ታዘዘ፣*
> 2. *ጎንደር አዘዞ ላይ በተመሳሳይ በሐሰት የብድር ውል ሽፋን ወደ ከተማ ክልል የገቡ ነገር ግን ያልተሸነሸኑና አሁንም በገጠር ቀበሌዎች የሚታወቁ አርሶ አደሮች ለእርሻ እየተገለገሉባቸው ያሉ*

*የገጠር መሬቶች ላይ አነስተኛ ጎጂዎችን በማቆም ለብድር ማስፈፀሚያት እንዲውሉ ፍርድ ቤቱ በበርካታ መዝገቦች ውሳኔ ሰጥቷል፡፡*

*በክልሉ መንግስት የወጣው የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ማስፈፀሚያ ደንቡ አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን ለምን ለምን ጉዳይ ሊገለገልበት እንደሚችል እና የባለይዞታነት መብቱን መቼ እና በምን ሁኔታ ለሌላ ሊያስተላልፍ እንደሚችል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በአምስት እና አስር ቆርቆሮ ዶርም እየተሠራ እስከ 1000 ካሬ ሜትር የገጠር መሬት በብድር ሽፋን ሲሸጥ ፍርድ ቤቱም ይህንን ሕገ ወጥ ተግባር ሲያስተናግድ ይውላል፡፡ ፍርድ ቤቱ በ2003 ዓ/ም ካስተናገድናቸው የፍትሐ ብሔር ጉዳዮ አብዛኛዎቹ በብድር ሽፋን የገጠር መሬት ሽያጭን የሚመለከቱ ሲሆኑ በ162 መዝገቦች ከ68,000 ካሬ ሜትር በላይ የገጠር መሬት ተሸንሽኖ ተሸጧል፡፡ በአጠቃላይ የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ በሕገ-መንግስቱ እና በዝርዝር ሕጎች በተቀመጡት መርሆዎች መሠረት ጉዳዮችን በማስተናገድ ውሰን የሆነውን ሐብት ለታሰለመለት ዓላማ እንዲውል በማድረግ ረገድ ችግሮች ነበሩ፡፡* ይላል የጥናቱ ውጤት፡፡[84]

ሕገ ወጥ ዉሎችን እዉቅና መስጠትን በተመለከተ ሌላ አንድ ምሳሌ እንድመለከት፡- አባቱ ከተማና ሞላ ግዛቸዉ በላይ አርማጭሆ ወረዳ ፍርድ ቤት ጀምረዉ በሚከራከሩበት መዝገብ[85] የስር ከሳሽ በአዋሳኝ የተጠቀሰ 2 ቃዳ መሬቴን ተከሳሽ 310 ብር ሲያበድረኝ መያዣዮያ አድርጌዉ የነበረ ቢሆንም አሁን ገንዘቡን ልመልስልህ መሬቴን ስጠኝ ብለዉ ፈቃደኛ ስላልሆነ እንዲመልስልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ 360 ብር ለከሳሽ አበድሬያት መመለስ ባለመቻሏ መሬቱ በገንዘቡ ተገምቶ በ1992 ዓ/ም በተፃፈ ውል ያስረከበችኝ ስለሆነና ከ10 አመት በላይ ስለሆነዉ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ግራ ቀኙ ያደረጉት ዉል ስለሆነ ውልን ለማስፈጸም ወይም ለማፍረስ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በ10 አመት ውስጥ ስላልቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብትጠይቅም የሥር ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ቅሬታዋን ስርዞታል፡፡[86]

ይሁን እንጅ የአማራ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ሕገ ወጥ ዉል ከመሆኑ አኳያ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት አቤቱታዉ ያስቀርባል ብሎ ግራቀኙን አከራክሮ በግራቀኙ መካከል ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬቱ በዕዳ ወይም በሽያጭ ተይዟል የሚል ከመሆኑ አኳያ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 40(3) መሠረት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑ ስለተደነገገ የግራ ቀኙ ስምምነት ህገ-ወጥ ነው፡፡ ህገ-ወጥ ውል ደግሞ በይርጋ ሊታገድ የማይገባ መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 14 የመ/ቁ 79394 አስገዳጅ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት መወሰናቸዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ብይኑን ሽሮ በፍሬ ነገር አከራክሮ እንዲወስን ለወረዳ ፍርድ ቤቱ መልሶለታል፡፡[87]

---

[84] *የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የ2003 ዓ/ም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ የቀረበ ጥናት፣ ጥቅምት 2004 ዓ/ም* ፣ ገፅ 15

[85] *የላይ አርማጭሆ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 01-05096፣ ሐምሌ 15/2005 ዓ/ም*

[86] *በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 117262፣ ሐምሌ 22/2005 ዓ.ም*

[87] *አባቱ ከተማ እና ሞላ ግዛቸው፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 33710* ጥቅምት 25/2007 ዓ.ም

በመሰረቱ መሬት መሸጥ መለወጥ እና ከዚሁ ጋር የተያያዙ በወለድ አገድ ወይም ለእዳ ማስያዥያ ማድርግ ወይም ለፍርድ አፈጻጸም ማዋል በኢፌዴሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ተከለከለ ነዉ።።[88] ይህን ተላልፎ መሰል ድርጊቶችን መፈጸም ሕገ ወጥ ድርጊት ነዉ።። ከላይ ከተጠቀሰዉ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይና በኦሮሚያ ክልል ጉፋ ወረዳ ጀምሮ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተሰጠበት ጀማል አማንና ተዋበች ፈረዴ በተከራከሩበት ጉዳይ[89] የሰበር ችሎቱ የገጠር መሬትን በወለድ አገድ ለእዳ ዋስትና አድርጎ መያዝ መሬት የመሸጥና መለወጥ ውጤት ስለሚኖረው ሕገ ወጥ ተግባር መሆኑን እና ሕገ ወጥ ዉል ደግሞ በይርጋ ሊታገድ የማይገባ መሆኑን በመተንተን ወስኗል።። በተመሳሳይ ሁኔታ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሬት በፍትሐ ብሔር ግንኙነት ለተፈጠር የእዳ መክፍያ ሊውል የማይችል ስለመሆኑና ሕገ ወጥ ዉል ከሆነ ዳኞች በማንኛዉም ጊዜ ይርጋም ሳያግደዉ ማፍረስ የሚችሉ መሆኑን ሌሎች ዉሳኔዎች ሰጥቷል።።[90] ከዚህ አንጻር ፍርድ ቤቶች በገጠር መሬት ዙሪያ ክርክሮችን ሲያከራክሩና ሲወስኑ ሕገ ወጥ ዉልን ወይም ግንኙነትን እዉቅና የሚሰጥ ሕገ ወጥ ዉሳኔ እንዳይሰጡ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።።

### 2.5 የገጠር መሬት ሕጎች የተፈፃሚነት ወሰን (ወደ ኋላ ተመልሰዉ ተገባራዊ እንዲሆኑ የማድረግ) ችግር

የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ቀደም ሲል በነበረው ስርዓት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቀጥሎ በደርግ ዘመን በአዋጅ ቁጥር 31/67 በኋላ ደግሞ በፌዴራል ደረጃ አዋጅ ቁጥር 89/1989 እና አሁን ያለው አዋጅ ቁጥር 456/1997 ወጥቷል።። በክልላችንም አዋጅ ቁጥር 16/1989 (የመሬት ሽግሽግ የተደረገበት አዋጅ)፣ አዋጅ ቁጥር 46/1992፤ አሁን በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ማስፈፀሚያ ደንቡ ቁጥር 51/1999 ወጥተዋል።። እነዚህ ሁሉ ሕጎች እንደየዘመናቸው ለመሬት ባለይዞታዎች የተለያየ መብት ይሰጣሉ።። ለመሆኑ በ1987 ዓ/ም የሞተ ሰው ቢኖር እና ወራሾቹ በ2000 ዓ/ም የውርስ ይገባኛል ጥያቄ ቢያቀርቡ በየትኛው ሕግ መሠረት ይወሰናል? በ1991 ዓ/ም የሞተ ቢሆንስ? በ1995 ዓ/ም ቢሆንስ? በመጨረሻ 1999 ዓ/ም የሞተ ቢሆንስ? የሚሉት ጥያቄዎች ይነሳሉ።

በመሰረቱ በሕግ አዉጭዉ አካል በግልጽ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ካልታተዘዘ በስተቀር[91] አንድ ሕግ ተግባራዊ የሚደረገዉ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ።። የኮመን ሎው ተሞክሮ የሚያሳየው በልዩ ሁኔታ በሕግ አውጪው ወይም የሕግ ትርጉም በሚሰጠው የበላይ ፍርድ ቤት ካልተወሰነ በስተቀር መርሁ ሕጎች ወደኋላ ተመልሰው ተፈፃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚል ነው።።[92] ሕግ አውጪው ወይም የበላይ ፍርድ ቤቶች ግን አንድ ልዩ ዓላማ ለማሳካት ወደኋላ ተመልሶ ተፈፃሚ የሚሆን ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ።። በአንፃሩ በሲቪል ሎው ተሞክሮ በሕግ አውጭው ካልተደነገገ በስተቀር ሕጎች ወደኋላ ተመልሰው ተፈፃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚለው መርህ ከፍ ያለ ተቀባይነት ያለው ከመሆኑም በላይ ሕግ አውጭው በልዩ

---

[88] የኤፌዴሪ ሕገ መንግስት፣ አንቀፅ 40 (3) እና አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀፅ 5(1)

[89] *ጀማል አማን እና ተዋበች ፈረዴ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ (ቅፅ 13) ፣ መ/ቁ 69291፣ ህዳር 08/2004 ዓ/ም*

[90] *ጋሻው በንሰው እና አለበል መከተ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት (ቅፅ 11)፣ መ/ቁ 49200፣ ህዳር 01/2003 ዓ/ም፤ አብደላ ኢብራሂም እና ኡሶ አብዲ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት (ቅጽ 14)፣ መ/ቁ 79394፣ ጥቅምት 06/2005 ዓ/ም*

[91] ለምሳሌ *የፍትሐ ብሔር ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 639/2001፣* አንቀፅ 3፣ በፍ/ሕ/ቁ 1723 ላይ የተደረገዉ ማሻሻያ ለባንኮችና ለፋይናንስ ተቋማት ሕጉ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ታወጀል።።

[92] በሪሁን አዱኛ ምህረቱ፣ *የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ የተፈፃሚነት ወሰን ከኒዚ አንፃር፡- በፍርዶች ላይ የቀረበ ትችት፣ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 4፣ ቁጥር 2፣ 2007 ዓ/ም፣ ገጽ 2 - 5*

ሁኔታ ወደኋላ ተመልሶ ተፈፃሚ የሚሆን ሕግ ለማውጣትም ጥብቅ መስፈርት እንዲያሟላ (ለምሳሌ በጣም አስፈላጊ የህዝብ ጥቅም) የሚጠበቅበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡[93]

ስለሆነም በሕግ አውጭው አካል በግልጽ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ካልተደነገገ በስተቀር አንድ ሕግ ተግባራዊ የሚደረገው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ የሚለው አጠቃላይ የሕግ አወጣጥ መርህ ነዉ፡፡ ሕጎቹ የሚጸኑበትንና ሥራ ላይ የሚዉሉበትን ሁኔታ የሚደነግጉበትን የሕጎችን ደንጋጌ ስንመከትም ይህን ሀሳብ አጉልተዉ ያሳዩናል፡፡ በዚህ መሰረት የገጠር መሬትን የተመለከቱ ሕጎች በእየዘመኑ የሚሰጡት ሙበት በሕግ አዉጭዉ የተለያዩ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ የአዋጅ ቁጥር 46/1992 እና የአዋጅ ቁጥር 133/1998ን ተፈጻሚነትና ይዘት ብንመለከት አዋጅ ቁጥር 133/98 ከግንቦት 21/1998 ዓ/ም ጀምሮ የፀና እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ከዚያ በፊት ደግሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከተሻረበት ጊዜ ተፈጻሚነት የነበረው አዋጅ ቁጥር 46/1992 ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት አዋጆች መሰረት የመሬት ባለይዞታ የሚሆንበት፣ መሬት የሚተላለፍብት እና መሬት የሚታጣበት ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸዉ። ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 46/1992 መሰረት የገጠር መሬት ባለይዞታ ከአንዱ ወደ አንዱ የሚተላለፈዉ ለቤተሰብ አባል ወይም ለጧሪ ተንከባካቢ ብቻ (ለቤተሰብ አባል በውርስ፣ ለጧሪ ተንከባካቢ በኑዛዜ) ነዉ፡፡[94] በአዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/1999 ግን መሬት በስጦታ፣ በውርስ (በኑዛዜና ያለኑዛዜ) ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ይተላለፋል፡፡ በዉርስ ከቤተሰብ አባል ዉጭ ለልጆችና ለወላጆች ሁሉ ሊተላለፍ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡[95]

ከዚህ ስንነሳ አዋጅ ቁጥር 46/1992 ተፈጻሚ በነበረበት ወቅት የሞተ ሰዉ የመሬት ዉርስ ሲተላለፍ ወራሹ የቤተሰብ አባል ካልሆነ ልጅ በመሆን ብቻ አይወረስም። ልጅ ሆኖም መሬት ቢኖረዉ ሊወርስ አይችልም፡፡ ይህም ሟች በሞተበት ዘመን ከነበረዉ ሕግ አንጻር ሲታይ በፍ/ሕ/ቁ 826(1) አንድ ሰዉ ሲሞት በሞተበት ስፍራ በሞተበት ቅፅበት ሊተላለፍ የሚችሉት ሙበቶቹ ወደ ወራሾች ይተላለፉሉ ከሚለዉ ድንጋጌ ጋር የሚሄድ ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር የገጠር መሬት ዉርስ የሚጠይቅ ሰዉ አዉራሹ በሞተበት ዘመን ከሚኖረዉ ሙበት አንጻር እየታየ ሲሰራ ቆይቷል፡፡[96]

ሆኖም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፋሲካ ሰጠኝና ገብሬ ሙስጠፋ በተከራከሩበት መዝገብ[97] "...ምንም እንኳን የአመልካች አዉራሽ እና ወላጅ እናት አሁን ስራ ላይ ያለዉ የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 ከመዉጣቱ በፊት 1991 ዓ/ም የሞቱ ቢሆንም ... ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ ለሆነዉ ጉዳይ አግባብነት የሚኖረዉ የተሻረዉ የፌደራል መንግስቱ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 89/1989 ሳይሆን አዲሱ የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 መሆን ይገባዋል..." በማለት ወስኗል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እምነት በበርካታ ምክንያቶች በሰበር ችሎቱ የተያዘዉ አቋምና የተሰጠዉ ትርጉም ተገቢ አይመስልም።

---

[93] ዝኒከማሁ፣ ገጽ 6 እና 7

[94]የቀድሞው *የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አመቃቀም አዋጅ ቁጥር 46/1992*፣ አንቀፅ 5

[95] አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀፅ 16 እና ደንብ ቁጥር 51/99፣ አንቀፅ 11(7)

[96]*ለምሳሌ አዲሱ አዝመራዉ እና እነ አብነህ ከልካይ (2 ሰዎች)፣ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 07219፣ ጥቅምት 16/2004 ዓ/ም፤ ያዳም ሞላ እና ታምራት ሞላ፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 48893፣ መጋቢት 21/2004 ዓ/ም፤ ሙሉ ንጋቱ እና አገር አባተ፣ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 25210፣ ጥቅምት 27/2005 ዓ/ም።*

[97]*የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 96395፣ ሚያዚያ 24/2006 ዓ/ም፤* እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎቱ *መሀመድ በላይ እና እነ እሸቱ ኢደም (2 ሰዎች)*፣ በመ/ቁ 86089፣ ሐምሌ 05 ቀን 2005 ዓ/ም በሚለው መዝገብ ተመሳሳይ ትርጉም ሰጥቷል።

አንደኛ እራሱ የሰበር ችሎቱ አቋሙ ወጥ ያልሆነ እና በሌላ ቄስ ሰሜ በላይ እንው እና አቶ ፋሲካዉ ሻምበል በተከራከሩበት መዝገብ[98] የቋሪት ወረዳ ፍ/ቤት አዋጅ ቁጥር 89/1998ን መሰረት አድርጎ (እንደሰበር ችሎቱ አባባል የተሸረውን አዋጅ) አከራከሮና አጣርቶ እንዲወስን የመለሰ መሆኑ ነዉ፡፡ ከላይ እንደተገለፀዉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 96395 እና 86089 ግን የሰር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ የሻረዉ አዋጅ ቁጥር 89/1989 የተሸረ አዋጅ ስለሆነ ተግባራዊ ሊደረግ አይገባም፤ አሁን ስራ ላይ ባለዉ አዋጅ ይወሰን በሚል ነበር፡፡

ሁለተኛ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድ ሰዉ ሲሞት ከፍ/ሕ/ቁ 826(1) አንጻር በሞተበት ወቅት በሕግ እዉቅና የተሰጠዉ መብት ብቻ ነዉ ሊያስተላልፍ የሚችለዉ፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ በ1994 ዓ/ም የሞተ ሰዉ ለወራሹ የሚያስተላልፈዉ የገጠር መሬት መብት በጣም የተገደበና ለቤተሰብ አባል (ምንአልባት በኑዛዜ ለጧሪ ተንከባካቢ ጭምር) ብቻ ነዉ፡፡ ከዘመናት በኋላ ሰፊ መብት የሚሰጥ ሕግ ስለወጣ ብቻ ሟች ሳያስተላልፈዉ የሞተዉንና ያልነበረዉን መብት ከሞተ በኋላ በተሰጠ መብት ለዚያዉም ሕጉ ከወጣበት ጊዜ ወደኋላ ተመልሶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ማለት ምክንያታዊም ህጋዊም አይደለም፡፡

ሶስተኛ የቀድሞቹ የገጠር መሬት አዋጆች ጠባብ መብት የሚሰጡ ስለነበር መሬቶቹ የሙተ ከዳ  ወይም ወራሽ የሌላቸዉ እተባሉ (ልጅ በመሆን ብቻ ስለማይወረስ ልጅ ያላቸዉ ሟቾች ቢኖሩም) መሬት ለሌላቸዉ ወጣቶችና ለተለያዩ ተቋማት ተሰጥተዉ ምናልባትም አንዳንዶቹ ከፍተኛ ለዉጥና ልማት ተሰርቶባቸዉ ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን ስራ ላይ ያለዉ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ ይስራ፣ ዱሮ መብት የሌለዉ ወራሽ አሁን ሊጠየቅ ይችላል የሚል አቋም ከተያዘ  አለመረጋጋትና ምስቅለቅሉ የበዛ ቀዉስ የሚያስከትል ይሆናል፡፡

አራተኛ የቀድሞዎቹ ሕጎች የተሸሩ ናቸዉ የሚባሉት ከተሸሩበት ጊዜ በኋላ ለሚከሰቱ ክስተቶች እንጅ በስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ያስተላለፉትና የሰጡት መብት ቀሪ የሚሆን ወይም የሚለወጥ አይደለም፡፡ ሕጎቹ ከተሻሩ በኋላም ቀድሞ ያልነበረ አዲስ መብት ሊሰጡ አይችሉም።

ስለሆነም ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሚያስከትለው ቀውስ ግምት ውስጥ ገብቶና የሕግ አወጣጥ መርሆዎችን ተከትሎ በፍጥነት ካልተስተካከለ በስተቀር ለአሰራር አስቸጋሪ እንደሚሆን ከፍ ያለ ቀውስ የሚያመጣ መሆኑን መገመት አያዳግትም።

### 2.6 ከይርጋ ጋር ተያይዞ የነበሩ ችግሮችና የተሰጠ መፍትሔ

ቀደም ሲል በነበረው አሠራር የመሬት ክርክር በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለው ሀሳብ አከራካሪ ነበር። በፍርድ ቤቶች ዘንድም ሁለት አይነት አቋሞች ነበሩ። የመጀመሪያው የመሬት ክርክር በይርጋ ሊታገድ አይገባም የሚል ነው። ይህን አቋም የሚያራምዱ ዳኞች መነሻ ሀሳባቸው ይርጋ ለአንዱ ወገን መብቱን ቀሪ አድርጎ ለሌላው ወገን መብት የሚያጎናጽፍ በመሆኑ የመሬት ክርክር በይርጋ ይታገዳል ማለት መሬት ከሚገኝባቸው መንገዶች (ድልድል፣ ስጦታ ወይም ኑዛዜ) ውጭ ተከሳሽ የሆነ ወገን መሬት እንዲያገኝ የሚያደርግ ስለሆነ ውጤቱ ሕገ ወጥ ይሆናል። የውርስ ክርክር ካልሆነ በስተቀር (የአንዱ ወራሽ መብት ታግዶ ለሌላኛው ወራሽ ቢተላለፍ ሕገ ወጥ ስለማይሆን) በሌላ መንገድ የሚደረግ የመሬት ክርክር

[98] *የመ/ቁ 85863፣ ሚያዚያ 09/2005 ዓ/ም*

በይርጋ ሊታገድ አይገባም የሚል ነው።[99] በሌላ አገላለጽ መሬት ከሌላ ንብረት የተለየ ሆኖ በተፈጥሮ የሚገኝ መተኪያ የሌለው ሀብት በመሆኑ ሰዎች እንደፈለጉ የሚይዙት ሳይሆን በመንግስት ጥብቅ ቁጥጥር ሥር ሆኖ በተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ የሚያዝ በመሆኑ በይርጋ ሰበብ ይህን ውድ ሀብት መያዝ ወይም ማግኘት አይቻልም የሚል ነው። ለዚህ አቋም ማጠናከሪያ የሚደረገው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 12(1)(ለ) መሰረት የመሬት ባለይዞታው ያለበት ቦታ ሳይታወቅና መሬቱን ሳያከራይ ወይም የሚያስተዳድርለት ሰው ሳይመድብ በተከታታይ ከ5 ዓመት በላይ ከመኖሪያ ቦታው የጠፋ እንደሆነ መብቱ ቀሪ ተደርጎ መሬቱ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ እንጅ መሬቱን በሆነ አጋጣሚ የያዘ ማንኛውም ሰው ባለይዞታው ሲከሰው የይርጋ ጊዜ ካለፈው እንዳይጠየቅ በሚል ሀሳብ የተቀመጠ አይደለም የሚለውን ነው።

ሁለተኛው ሀሳብ መሬት እንደማንኛውም ክርክር የይርጋ ጊዜ ሊኖረው ይገባል የሚል ሲሆን የይርጋ ዘመኑን በተመለከተ አንዳንዶች የፍ/ሕ/ቁ 1149ን በመውሰድ በ2 ዓመት ሌሎች ደግሞ ቁጥር 1845ን በመውሰድ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል የሚል አቋም ነበራቸው። የመሬት ክርክር በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሶስት አስገዳጅነት ያላቸው ውሳኔዎችን ሰጥቷል።

የመጀመሪያው በወራሾች መካከል የሚደረግ የመሬት ክርክር በፍ/ሕ/ቁ 1000(1) መሰረት በሶስት አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የወሰነበት *የበርገና ሸፈራው እና እነ አብርሀም ሸፈራው* ጉዳይ ነው።[100] ይኸውም ተጠረዎች አመልካች የሚች አባታችን የውርስ መሬት ስለያዘ ያካፍለን በማለት ክስ ሲያቀርቡበት አመልካች ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያ ቢያነሳም በእየደረጃው ያሉት የሥር ፍርድ ቤቶች ስለይርጋው ምንም ሳይሉ በማለፍ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጥተዋል። ሆኖም የፌዳራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት የግራቀኙ አባት ከሞቱ ከ26 አመታት በኋላ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ 1000(1) መሰረት ከሳሽ መብቱንና የውርሱን ንብረቶች በተከሳሽ መያዛቸውን ካወቀ 3 አመት ካለፈ በኋላ ስለወራሽነት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ስለማይኖረው ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ወስኗል። ይህን ውሳኔ የመሬት ክርክር ይርጋ ሊኖረው አይገባም በማለት የሚከራከሩት ዳኞችም ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ። ምክንያቱም በወራሾች መካከል የአንዱ ወራሽ መብት ታግዶ ሌላው ወራሽ ጠቅልሎ መሬቱን ቢወርሰው መሬት ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንጻር ችግር ስለማይኖረው ነው።

ሁለተኛው ወራሽ በሆኑና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ የገጠር መሬት ክርክር በፍ/ሕ/ቁ 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የተወሰነበት የሸለማ ነገሰ እና ፋይሳ መንግስቱ ጉዳይ ነው።[101] ተጠሪ የአባቱን የውርስ መሬት እንዲለቅላት በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብበት አመልካች መሬቱን ለ18 ዓመት የያዝኩት ስለሆነ ክስ ሊያቀርብብኝ አይገባም የሚል መቃወሚያና የፍሬ ነገር መከራከሪያ አቅርቧል። በእየደረጃው ያሉት የሥር ፍርድ ቤቶችም የይርጋ ክርክሩን እልባት ሳይሰጡ በፍሬ ነገሩ ላይ ወስነዋል። በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በሚከተለው መልኩ አትቷል።

---

[99] ለምሳሌ እነ ይታክቱ አለምነህ (2 ሰዎች) እና እነ ሳሴ አለምነህ (2 ሰዎች)፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 48853፣ መጋቢት 11/2004 ዓ/ም የተሰጠውን ትንታኔ መመልከት ይቻላል።

[100]በርገና ሸፈራው እና እነ አብርሀም ሸፈራው(4 ሰዎች)፣*ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት (ቅፅ 09)፣ መ/ቁ 38237፣ ታህሳስ 21/2001 ዓ/ም*

[101]ሸለማ ነገሰ እና ፋይሳ መንግስቱ ሰዎች)፣ *ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣* ቅጽ 13፣ መ/ቁ 69302፣ ታህሳስ 20/2004 ዓ/ም

*ማንኛውም አርሶ አደር ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የእርሻ መሬት ላይ ያለውን የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር ተገቢውን ትጋት የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል። [በሌሎች የይርጋ የጊዜ ገደብ በግልጽ ባልተደነገገላቸው ጉዳዮች በፍ/ሕ/ቁ 1677(1) እና 1845 የተደነገገው የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ከመወሰኑም በላይ አርሶ አደሮች በሕገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብትን በፍርድ ከሰው ለማስከበር ሰፋ ያለ እድል ስለሚሰጥ ከገጠር መሬት ሕጎች መሰረታዊ መርሆዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ይዞታውን በሌላ ሰው የተነጠቀ አርሶ አደር ወይም ወራሾቹ ይዞታው በሌላ ሰው ከሕግ ወይም ከውል ውጭ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአስር አመት ውስጥ የእርሻ መሬት የባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ካላቀረበ ክሱ በፍ/ሕ/ቁ 1677(3) እና 1845 በተደነገገው የአስር አመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰናል። ... ስለሆነም ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በማለፍ መሬቱን ለተጠሪ እንዲለቅ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።]*

በመሰረቱ የዚህ ውሳኔ ይዘት መሬቱን በሆነ ምክንያት ለያዘ ሰው የትክክለኛው ባለይዞታ መብት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ ሲወሰን መሬት ከሚገኝባቸው መንገዶች (ከድልድል፣ ውርስና ስጦታ) ውጭ በሌላ መንግድ መሬት እንዲይዝ ወይም እንዲያገኝ ያስችለዋል። በእርግጥ መሬቱን የያዘው ሰው የቀረበበት ክስ በይርጋ ቢታገድም የመሬቱ ባለቤት የሆነው መንግስት በፈለገው ጊዜ መሬቱን ተገቢ ባልሆነ መንገድ የያዘውን ሰው ከሶ ማስለቀቅ ይችላል የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። ይሁን እንጅ የመሬቱ ባለይዞታ መሬቱን ጥሎ በመጥፋቱ ወይም ያለበት ሳይታወቅ ወይም ሳያከራየው ከአምስት አመት በላይ በመጥፋቱ መንግስት በሕጉ መሰረት መሬቱን ሳያነሳው ከዘገየ መሬቱን ያለ ሕጋዊ መንገድ ይዞ ክሱ በይርጋ ይታገድልሀል ከሚባለው ሰው ይልቅ የመሬቱ ባለይዞታ የነበረው ሰው መንግስት እስኪቀመው ድረስ የመጠቀም የተሻለ መብት ይኖረዋል። በሌላ አገላለጽ መሬቱን ተገቢ ባልሆነ መንገድ የያዘው ሰው የመሬቱ ባለይዞታ ክስ ሲያቀርብበት ከመሬት ሕጉና ፓሊሲ አንጻር መሬቱን ይዞ ለመቀጠል ሕጋዊ መከራከሪ ያሊኖረው አይችልም።

ሶስተኛው ደግሞ መንግስት በመሬት ላይ የሚያቀርበው ክስ በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ *በግሸ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ጌጤ ተፈራ ጉዳይ* የተሰጠው ውሳኔ ነው።[102] አመልካች በተጠሪና በወንድሟ ተሾመ ተፈራ ላይ የራሳቸው በቂ መሬት ያላቸው ስለሆነ የአባታቸውን መሬት ደርበው ስለያዙ ሊለቁ ይገባል የሚል ክስ ሲያቀርብባቸው የወረዳውና የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክረው ወስነዋል። የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 69302 የሰጠውን ውሳኔ በመጥቀስ ተጠሪ የሚች አባቷን መሬት ከአስር አመት በላይ የያዘች ስለሆነ የአመልካች ክስ በአስር አመት ይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኗል።[103] በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳየን በመጨረሻ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

[102]የግሸ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ጌጤ ተፈራ፣ *ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት*፣ መ/ቁ 93013፣ ጥር 30/2006 ዓ/ም

[103]ጌጤ ተፈራ እና የግሸ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣ *የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት*፣ መ/ቁ 28536፣ ግንቦት 26/2005 ዓ/ም

ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መንግስት የሚያቀርበው የመሬት ክስ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን በሚከተለው መልኩ ተንትኖታል።

> *[… አመልካች የመሬት ይዞታው ሊለቀቅልኝ ይገባል የሚለው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(3) እና በመሬት አዋጆች የተሰጠውን መሬትን በባለቤትነት የማስተዳደር ሀላፊነትና ተግባር መሰረት ነው። … ከመ/ቁ 69302 ውሳኔ ይዘት በግልጽ መረዳት የሚቻለው ችሎቱ በመሬት ላይ የይዞታ መብት አለኝ በሚሉ ወገኖች መካከል ለሚነሳ ክርክር የይርጋው ጊዜ አሰር አመት መሆኑን ከመወሰኑ ውጭ የመሬት ባለቤት የሆኑትን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችንና መንግስትን ወክሎ በመሬቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ለመጠቀም መሬቱን ለማስተዳደር የሚችል አካል የይዞታ መብት አለን በሚሉ ሰዎች ላይ የሚያቀርበውን ክሰ ሁሉ የሚያጠቃልል ያለመሆኑን ነው። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተከራከሪ ወገኖች ማንነትና በአከራካሪ መሬቶቹ ላይ ያላቸውን የመብት ኢይነቶችና ኢድማሳቸውን ሳይለይ የይዞታ መብት ብቻ አለን በሚሉ ሰዎች መካከል በተነሳ ክርክር ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያለቦታው ጠቅሶ የአመልካች ክሰ በአሰር አመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።]*

በአጠቃላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከመሬት ጋር የተያያዙ ክርክሮችን በተመለከተ በወራሾች መካከል የሚደረግ ከሆነ በፍ/ሕ/ቁ 1000(1) መሰረት በሶስት አመት፣ ወራሽ በሆኑና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ሲወስን መንግስት የመሬት ባለቤት በመሆኑ በመሬት ላይ የሚያቀርበው ክስ በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት አስገዳጅነት ያላቸው ትርጉሞችን መስጠቱን መረዳት ይቻላል። በጸሐፊው እምነት አንደኛውና ሶስተኛው የሰበር ውሳኔዎች ላይ የተሰጠው ትርጉም ተገቢነት ያለው በመሆኑ አከራካሪ አይደለም። ሆኖም በሁለተኛው ውሳኔ (የሸለማ ነገሰ እና ፋይሳ መንግስቱ ጉዳይ) ላይ የተሰጠው ትርጉም ከላይ በተገለጸው መሰረት መሬት ከሚገኝባቸው (ከሚያዝባቸው) መንገዶች አንጻር ሲታይ ተገቢነቱ አከራካሪ ነው። ስለሆነም እነዚህ ትርጉሞች ከመሰጠታቸው በፊት የነበረውን ውዝግብ የሰበር ችሎቱ ያስቀረ ቢሆንም የውሳኔዎቹ ተገቢ መሆን አለመሆን ጉዳይ ግን ራሱን በቻለ ጥናት የሚመለስና ለውይይት ክፍት የሆነ ነው።

## ማጠቃለያ

አለመግባባት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተት በመሆኑ ሁልጊዜም የማይቀር ጉዳይ ነው። በተለይ በገጠር መሬት ዙሪያ የሚከሰቱ አለመግባባቶች በርካታ መሆናቸውን በፍርድ ቤቶች ከሚቀርቡ ክርክሮች አብዛኛዎቹ የመሬት ጉዳይ መሆናቸውን በማየት ብቻ መረዳት ይቻላል። በዚህ ጽሑፍ ከገጠር መሬት ይዞታ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች ሲከሰቱ የሚፈቱባቸውን መንገዶች ተመለከተናል።

አማረጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ፈጣን፣ ወጭ ቆጣቢና ባለጉዳዮችን አሳታፊ እንዲሁም መልካም ግንኙነታቸው ዘለቄታ እንዲኖረው የሚያደረግና ሁለቱንም ወገኖች ውጤታማ ስለሚያደርግ ተመራጭነት አለው። የክልላችን የገጠር መሬት የሕግ ማዕቀፍም በተቻለ መጠን የገጠር መሬት አለመግባባት በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች እንዲያልቅ ጥረት መደረግ ያለበት መሆኑን ያስገነዝበናል። በእርግጥ ባለጉዳዮች አለመግባባቱን በዚህ መልኩ ካልጨረሱ ወይም ይህን ዘዴ መጠቀም ካልፈለጉ ክርክራቸውን መደበኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን ሕጉ ያስቀምጣል። ከዚህ አንጻር ተከራካሪዎች የአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን ጥቅም በመረዳት ጉዳያቸውን በዚህ መልኩ ቢጨርሱ ለእነሱም ሆነ ለፍትሕ ስርዓቱ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ሆኖም በተግባር ባለጉዳዮች አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን ከመጠቀም ይልቅ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት መምጣት የተለመደ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ከአቅም በላይ በሆነ የመሬት ክርክር ሲጨናነቁ ይታያሉ። ፍርድ ቤቶችም ክርክሩን በአግባቡ በመምራት ተገቢውን ጭብጥ መስርቶና በተገቢው ማስረጃ አጣርቶ ያለመወሰን እንዲሁም የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የሕግ ድንጋጌዎችን ይዘት ያለመረዳት እጥረቶች ያለባቸው መሆኑን ተመልክተናል።

በአጠቃላይ የክልላችን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የሕግ ድንጋጌዎችን ይዘት፣ አላማና ግብ ባለጉዳዮች አለመግባባቶች በተቻለ መጠን ጉዳያቸውን በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች እንዲፈቱ ጥረት መደረግ ያለበት መሆኑን፤ ይህ ዘዴ ውጤታማ ሳይሆኑ ሲቀረ ወይም ባለጉዳዮቹ ይህን ዘዴ ሳይፈለጉ ከቀሩ ክርክሩ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊቀጥል የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ባለጉዳዮች በቀጥታ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቶቸ ጉዳዩ በአመራጭ የሙግት መፍቻ እንዲያልቅ ሊያሳስቧቸው ይገባል። ከዚህ አልፎ ክርክሩ በፍርድ ቤት ከቀጠለ ዳኞች ከምንም በፊት የመሬት ሕጉን ይዘት፣ አላማና ግብ በአግባቡ በመረዳት ከፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ክርክሩን በአግባቡ በመምራትና ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ፣ በተገቢው ማስረጃ በማጣራት ተገቢነት ያለው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

## ዋቢዎች

### የተለያዩ ጽሑፎች


Adriana Herrera & Maria Guglielma da Passano, Land Tenure Alternative Conflict Management, Food and Agriculture Organization of the United Nations, Rome, (2006)

*ዓሊ መሀመድና ማሩ ባዘዘው፣ የመሬት ባለይዞታና ተጠቃሚ የመሆን መብት በኢትዮጵያ፣ ነሐሴ 2002 (ያልታተመ)*

Bengt Andersson, future Framework of Land Related Laws in Amhara National Regional State: Sida Amhara Rural Development Programme, (July 2005)

*በሪሁን አዱኛ ምህረቱ፣ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ የተፈፃሚነት ወሰን ከጊዜ አንፃር፡- በፍርዶች ላይ የቀረበ ትችት፣ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 4፣ ቁጥር 2፣ 2007 ዓ/ም*

_____ *የገጠርና የከተማ መሬትን የሚመለከቱ ህጐችና አፈጻጸማቸ በኢትዮጵያ* ፡ በፌዴራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም የተዘጋጀ (የካቲት 2004 ዓ/ም፣ ያልታተመ)

ብርሀነ አሰፋ፣ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓትና ህገ-መንግስቱ፣ *የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (2000ዓ/ም፣ ያልታተመ)*

Shipi M. Gowok, Alternative Dispute Resolution in Ethiopia' a Legal Framework, p. 266 - 268, avialable at *www.afrrevjo,net/journal/multi-dicipline/Vol/2/No/2/Art/17/GOWOK.pdf* (accessed on Junly 24/2014)

ደሴ ስዩም፣ *የገጠር መሬት ሕግጋትና እይጋጠሙ ያሉ ችግሮች፣* ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች የተዘጋጀ የስልጠና ጽሑፍ፣ ባህርዳር ዩንቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲቱት፣ (መስከረም/2006 ዓ/ም)

Molla Ababu & Worku Yaze, Materials on Law of Evidence: *Notes, Cases, and Questions, Bahir Dar & Jimma Universities* (2010)

ወርቁ ያዜ ወዳጅ፣ *በገጠር መሬት የይዞታ ክርክር ሂደት ትኩረት የሚያሻቸው የማስረጃ ሕግ ጉዳዮች*፣ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት እና የስዊድን የልማት ተራድኦ ድርጅት ድጋፍ ለወረዳ ፍ/ቤት ዳኞች ስልጠና የተዘጋጀ (ያልታተመ፣ መስከረም 2006 ዓ/ም)

*የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የ2003 ዓ/ም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ የቀረበ ጥናት፣ ጥቅምት 2004 ዓ/ም*

## ሕጎች

የኤፌዴሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ/ም

*የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1952 ዓ/ም*

*የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1958 ዓ/ም*

*የፍትሐ ብሔር ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 639/2001 ዓ/ም*

*የኢፌዴሪ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ዓ/ም*

የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 414/1996 ዓ/ም

*የገጠር መሬትን የህዝብ ሀብት ለማድረግ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 31/1967 ዓ/ም*
*የገበሬ ማህበራትን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 223/1974 ዓ/ም*

የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 20/1989 ዓ/ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 148/1999 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ/ም

*የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አመቃቀም አዋጅ ቁጥር 46/1992* ዓ/ም

*የተሻሻለው የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር133/1998* ዓ/ም

*የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ስርዓትን ለማስፈፀም የወጣ ክልል መስተዳደር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 51/1999*

*የአዋጅ ቁጥር 133/1998* እና የደንብ ቁጥር 51/1999 ማስፈጸሚያ መመሪያ

*የተሻሻለዉ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 ዓ/ም*
*የተሻሻለዉ የደቡብ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 ዓ/ም*
*የተሻሻለዉ የትግራይ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር136/2000 ዓ/ም*

## የፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች

በርገና ሽፈራው እና እነ አብርሀም ሽፈራው(4 ሰዎች)፣*ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት (ቅፅ 09)፣ መ/ቁ 38237፣ ታህሳስ 21/2001 ዓ/ም*

ሸለማ ነገሰ እና ፋይሳ መንግስቱ፣ *ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣* ቅጽ 13፣ መ/ቁ 69302፣ ታህሳስ 20/2004 ዓ/ም

የግሸ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ጌጤ ተፈራ፣ *ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት*፣ መ/ቁ 93013፣ ጥር 30/2006 ዓ/ም

*ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሸበሸ፣* የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ *ቅጽ 3፣ መ/ቁ 14554፣ ታህሳስ 20/1998 ዓ/ም*

*ጥላሁን ጎበዜ እና እነ መከተ ታይሉ (2 ሰዎች)፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ቅጽ 13፣ መ/ቁ 69821፣ ታህሳስ 17/2004 ዓ/ም*

*ሰሜ በላይ እንየው እና ፋሲካው ሸምላ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 85863፣ ሚያዚያ 09/2005 ዓ/ም*

*ካሳሁን ሀብቱና እናትፈንታ ቢረሳው፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 85128፣ የካቲት 29/2005 ዓ/ም*

*ጀማል አማን እና ተዋበች ፈረዴ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ቅፅ 13፣ ፣መ/ቁ 69291፣ ሀዳር 08/2004 ዓ/ም*

*ጋሻው በንሰው እና አለበል መከተ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ቅፅ ፲፣ መ/ቁ 49200፣ ሀዳር 01/2003 ዓ/ም፣*

*አብደላ ኢብራሂም እና ኡሶ አብዲ፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ቅጽ 14፣ መ/ቁ 79394፣ ጥቅምት 06/2005* ዓ/ም

*መሀመድ በላይ እና እነ እሸቱ ኡደም (2 ሰዎች)፣የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት* ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 86089፣ ሐምሌ 05/2005 ዓ/ም

*አዲሱ አዝመራዉ እና እነ አብነህ ከልካይ (2 ሰዎች)፣ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 07219፣ ጥቅምት 16/2004 ዓ/ም*

*ሙሉ ንጋቱ እና አገር አባተ፣ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 25210፣ ጥቅምት 27/2005 ዓ/ም።*

ጌጤ ተፈራ እና የግሸ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣ *የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት*፣ መ/ቁ 28536፣ ግንቦት 26/2005 ዓ/ም

*አባቱ ከተማ እና ሞላ ግዛቸው፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ መ/ቁ 33710* ጥቅምት 25/2007 ዓ.ም

*ያዳም ሞላ እና ታምራት ሞላ፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 48893፣ መጋቢት 21/2004 ዓ/ም*

እነ ይታክቱ አለምነህ (2 ሰዎች) እና እነ ሳሴ አለምነህ (2 ሰዎች)፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ መ/ቁ 48853፣ መጋቢት ፲፩/2004 ዓ/ም

የሰከላ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ዘመኑ ይርዴ፤ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ መ/ቁ 48849፣ መጋቢት ፲0/2004 ዓ/ም